# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 122 መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ለዘንድሮ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከ6 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተዘጋጅተዋል



• ባለፈው ክረምት ከተተከሉት ችግኞች 80 በመቶው ጸድቀዋል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ለዘንድሮ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር 6ነጥብ 7 ቢሊዮን ችግኞች መዘጋጀታቸውን የግብርና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የግብርና ሚኒስትር አቶ ኡመር ሁሴን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ለዘንድሮ ክረምት የችግኝ ተከላ ከመጠባበቂያ ጋር 6ነጥብ 7 ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል፡፡

ከእቅዱ በላይ የተዘጋጀው የሚበላሸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው ያሉት ሚኒስትሩ የችግኝ ዝግጅቱ የተጀመረው የባለፈው አመት ክረምት ችግኝ ተከላ እንደተጠናቀቀ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እየተዘጋጁ ያሉት ችግኞች ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ውስጥ የሚደርሱ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚው አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ የአትክልት እና ፍራፍሬ ዝርያ ያላቸው እንደ አቮካዶ የመሳሰሉ ዝርያዎች ከ 40 እስከ 50 በመቶ ድርሻ ይይዛሉ፡፡ የተቀሩት ለደን አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ችግኞች ናቸው፡፡

የተተከሉ ችግኞችን የጽድቀት ምጣኔ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚከታተልበት አሠራር እንዳለው የጠቆሙት ሚኒስትሩ፣ ባለፈው ዓመት ክረምት የተተከሉ ችግኞች ሁለተኛው ዙር ባይጠናቀቅም በመጀመሪያ ዙር ምልከታ ሰማንያ በመቶ መጽደቃቸውን ጠቁመዋል፡፡ የጽድቀት መጠኑ በመጀመሪያ ዓመት እና በሁለተኛ አመት የነበረው ከባለፈው አመት የበለጠ

ለዘንድሮ የችግኝ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ኤች.አር 6600 እና ኤስ 3199 ረቂቅ ሕጎችን ለማስቆም የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግሥት ጥሪ አቀረበ

ገጽ 4

# የሸብር ቡድኑ በበራህሌ፣ ኮነባና አብአላ አካባቢዎች ተኩስ በመክፈቱ ዕርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ሰመራ ለመቆም ተገደዋል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የሸብር ቡድኑ በበራህሌ፣ ኮነባና አብአላ አካባቢዎች ተኩስ በመክፈቱ የሰብዓዊ ዕርዳታ ጭነው ወደትግራይ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ሰመራ ከተማ መቆማቸውን የአፋር ክልል አመራሮች አስታወቁ።

የአፋር ክልል ኪልበቱ ረሲ ዞን /ዞን ሁለት/ የሎጂስቲክስ አስተባባሪ አቶ አብዱ መሃመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የአሸባሪው ሕወሓት ቡድን በአፋር ክልል ወረራ በመፈጸም በራህሌ፣ ኮነባና አብአላ አካባቢዎች ተኩስ ከፍቷል። ይህ የጥፋት ድርጊቱ የሰብዓዊ ዕርዳታ ጭነው ወደትግራይ ክልል ሊገቡ የነበሩ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ዕክል ፈጥሯል።



እንደ አቶ አብዱ ከሆነ፣ በርካታ የሰብዓዊ ዕርዳታ ማጓጓዣ የጭነት ተሽከርካሪዎችም ጦርነት በተከፈተባቸው አብዓላና ሌሎች የአፋር አካባቢዎች አልፈው ወደትግራይ ክልል መግባት አልቻሉም። በዚህ የተነሳ ዕርዳታ የጫኑ 20 ከባድ ተሽከርካሪዎች በሰመራ ከተማ ቆመዋል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በከፈተው ጦርነት የተነሳ በርካታ የአፋር ነዋሪዎች ተፈናቅለዋል ያሉት አቶ አብዱ፣ ይሁንና የትግራይ ሕዝብም የኢትዮጵያ አካል ነው በሚል ኅብረተሰቡ የሰብዓዊ ዕርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች እንዲያልፉ ትብብር ቢያደርግም የሸብር ቡድኑ በከፈተው ጦርነት የተነሳ ተሽከርካሪዎቹ አብዓላ እንኳን መድረስ አልቻሉም ብለዋል።

ቡድኑ በፈጠረው ግጭትና ጦርነት የተነሳ የሰብዓዊ ዕርዳታውን ወደትግራይ ማጓጓዝ ባይቻልም አሸባሪ ቡድኑ ግን የእራሱን ጥፋት ለመሸፋፈን መንግሥት ዕርዳታ ወደትግራይ እንዳይገባ አድርጓል የሚል ክስ በተደጋጋሚ ማቅረቡ ቡድኑ ውሸትን እንደአንድ የማደናገሪያ ስልት የሚጠቀምበት መሆኑን ያረጋገጠ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በአፋር ክልል የሚያደርገውን ጦርነትና ግጭት አባባሽ ድርጊቶች የሚያቆም ከሆነ ዕርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ያለምንም ችግር ወደትግራይ ክልል

የሸብር ቡድኑ በበራህሌ፣... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## መንግሥት በሳውዲአረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ 100ሺ ዜጎችን መመለስ ጀመረ

ገጽ 4







ዜና



# ኢትዮጵያ ስኬታማ አገራዊ ምክክር ካደረጉት ደቡብ አፍሪካና ሩዋንዳ ልምድ ልትቀስም ይገባል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ደቡብ አፍሪካና ሩዋንዳ ስኬታማ አገራዊ ምክክር ያደረጉት ገለልተኛ ኮሚሽን በማቋቋምና ችግራቸውን የለየ ሥራ በመሥራታቸው መሆኑን የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ ደጉ አስረስ (ዶክተር) ገለጹ። ኢትዮጵያም ከእነዚህ አገራት ልምድ መቅሰም እንደሚገባት ተናግረዋል።

የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ ደጉ አስረስ (ዶክተር) በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በደቡብ አፍሪካና ሩዋንዳ ስኬታማ ምክክር ያደረጉት የነበረባቸውን ችግር በትክክል ለይተው በመሥራታቸው ነው።

ደቡብ አፍሪካውያን በአፓርታይድ አገዛዝ ስር የነጮች ሥርዓት በጥቁሮች ላይ ከፍተኛ ግፍ የፈጽሙበት ነበር። ቅራኔውን ለመፍታት ታላላቅ አገሮች ዓለም አቀፍ ተቋማት ተሳትፈውበት ይቅር ተባብለው ወደ አንድነት እንዲመለሱ የተደረገበት ሲሆን ከመነጋገር፣ መመካከር ጀምሮ ያለፈውን ይቅር በመባባል ወደ ሰላም ግንባታ መግባታቸውን ተናግረዋል።

በሩንዋንዳም በኢንተርሀሞይ የተፈጸመውን የዘር ፍጅት ዕልባት ለመስጠት የእርቅና ድርድር ኮሚሽን ተቋቁሞ ለውጤት መብቃቱን ዶክተር ደጉ ጠቁመዋል።

እንደ ደጉ (ዶክተር) ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ያለችበት አውድ ሲታይ እና ሌሎች አገሮች ላይ ኮሚሽን የተቋቋመበት ሁኔታ የተለየ ነው። የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ከሌሎች አገሮች ጋር ሊወዳደርበት የማይችልባቸው ጉዳዮች አሉ። የሕዝብ ጠብና ቅራኔ የሌለበትና አሁንም በአንድነት የሚኖር ሕዝብ ነው።

ነገር ግን የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች ባላቸው ስልጣን ፍላጎት ስምምነት መፍጠር ባለመቻላቸው ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት በመሆኑ በሌሎች አገሮች ላይ ያለውን ተሞክሮ እንዳለ አምጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ላይሆን ይችላል። ከሌሎች አገራት ሊወሰድ የሚችለው ትምህርት ቁልፉ ጉዳይ ችግራቸውን ለይተው በመሥራታቸው ስኬታማ ምክክር ለማድረግ መቻላቸው ነው።

በኢትዮጵያ ቀደም ብሎ በተለያዩ ቡድኖች የአገራዊ ምክክር ጉዳይ ሲነሳ እንደነበር ያስታወሱት ምሁሩ፤ የእርቅና የድርድር ኮሚሽኑ ሲቋቋም ዋና ተልዕኮው ማንና ማን በምን ነው የሚታረቁት፣ የሚመካከሩት፣ በሚለው ላይ ግልጽነት አልነበረም።

በኢትዮጵያ ታሪክ ከስልጣን ፍላጎት የመነጨ የጥቅምና የመገንጠል ፍላጎት የሚያመጣው ግጭት እንጂ ሕዝብ የሚያመጣው ግጭት የለም። ለአብነትም የሕወሓትና የኦነግ ፍላጎት ሲታይ የስልጣን ጥያቄ አንስተው ሲዋጉ የኖሩ ስለመሆናቸው ገልጸዋል።

እስካሁን ያጠፉት ጥፋት እንዳለ ሆኖ ግጭት ትተው ወደ ሰላም እንዲመጡ፣ በልማትና ፖለቲካው መስክ በሰላማዊ መንገድ እንዲሳተፉ ማድረግ ካስፈለገ የምክክር ኮሚሽኑ የመወያያና የመደራደሪያ ሀሳቦችን በግልጽ እንዲወጡ ማድረግ ይጠበቅበታል።

# ሚዲያዎች በጋራ እሴቶች ላይ ትኩረት በማድረግ አገራዊ ምክክሩ ስስኬት እንዲበቃ ማድረግ አለባቸው

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ በአገራችን ሊካሄድ የታሰበው አገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን ሚዲያዎች በጋራ እሴቶች ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት እንዳለባቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ ምሁራን አስታወቁ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ሚዲያዎች አገራዊ ምክክሩን ስኬታማ ለማድረግ በጋራ እሴቶች ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ለማድረግ በሚዲያዎች የሚዘገቡ ዘገባዎች በሰዎች መካከል ያሉ መልካም ዕሴቶችና የጋራ ጉዳዮች ላይ ዋነኛ ማጠንጠኛቸው ሊሆን ይገባል።



ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ ሽፈራው



መምህር ሮባ ጴጥሮስ

እንደ ረዳት ፕሮፌሰሩ ገለጻ፣ ሚዲያዎች ሰዎች በባህላቸው፣ በእምነታቸውና በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ስለ ጋራ እሴቶቻቸው እንዲያስቡ የሚያደርግ የአዘጋገብ ዘይቤ መርጠው መቀራረብን መፍጠር አለባቸው። ሚዲያ ሰዎች አንድ ላይ እንዲያስቡ፣ተመሳሳይ አገራዊ ስሜትና ራዕይ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ አቅም አለው ብለዋል።

የተለያየ ብሔር፣ ኃይማኖት፣ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ፍላጎቶች፣ አመለካከቶች ባለበት አገር እንዴት ወደፊት በጋራ መሄድ እንደሚቻል ሚዲያ አቅጣጫ ማሳየት መቻል አለበት።

ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ ሽፈራው እንደሚሉትም የምክክሩን ሂደትና ከምክክሩ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለኅብረተሰቡ በማሳወቅ ኅብረተሰቡ አገራዊ ምክክሩን በሐሳብ እንዲደግፍ ማድረግ መቻል አለባቸው። ምሁራንም ሐሳብ እንዲያመነጩ በመጋበዝ የሕዝቦችን ተቀራርቦ አብሮ የመቀጠል ዕድል የማሳየት ሥራ መሥራት ከሚዲያ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሕግና ሠላም ልማት መምህር ሮባ ጴጥሮስ በበኩላቸው የአገራዊ ምክክሩ ሐሳቦችን ስኬታማ ለማድረግ ሚዲያ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዝ ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ የአገራዊ ምክክር ምንነት፣ የሚያካትታቸው አጀንዳዎቹን ተረድቶ በባለቤትነት መንፈስ እንዲሳተፍ ከሚዲያ ብዙ እንደሚጠበቅ ጠቅሰው፣ ገለልተኛና ሕጋዊ በመሆን አገራዊ ምክክር መድረኮችን የማመቻቸት አቅም አላቸው። ባለድርሻ አካላትና ተከታዮቻቸውን እንዴት ማሳመን እንደሚቻልም በትኩረት ሊሠሩበት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሚዲያ ገለልተኛና ሥነምግባር የተላበሰ መሆን አለበት ያሉት መምህሩ በተቃራኒው ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ አደጋው የከፋ መሆኑ የዓለም ተሞክሮ እንደሚያሳይ ገልጸዋል።

እንደ መምህር ሮባ ገለጻ ሚዲያ ተቋማት ከምሁራን ሐሳቦችን በመግዛትና በመሸጥ አገራዊ ምክክሩን ስኬታማ ማድረግ አለባቸው። የሕዝብ ግንኙነት ልማት፣ በጋራ እሴቶች ላይ ማተኮርና በቅንጅት መሥራት ለአገራዊ ምክክር የሚያስፈልጉ ነገሮች እንደሆኑ ገልፀው መሰል ጉዳዮችን በፍጥነት በመከታተል መዘገብ ከሚዲያ ተቋማት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

ከአገራት ከተሞክሮ አንጻር ሲታይ በአገራዊ ምክክር ላይ ብቻ የሚሠሩ ሚዲያዎች መኖራቸውን ጠቁሞ እንደ አገር የጋራ እሴቶቻችን ላይ ብቻ በማተኮር የሚዘግቡ ሚዲያዎች መኖር እንዳለበት መክረዋል። ኢትዮጵያም ይህንን ተሞክሮ ልትወስድ ይገባል።

# የደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ ከተተኪ ምርት ከ21ሚሊዮን ዶላር በላይ ማግኘቱን አስታወቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ደብረ ብርሃን፡- ባለፉት ስድስት ወራት ከተተኪ ምርቶች (ኢምፖርት ሰብስቲቲዩሽን) ከ21 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ማግኘቱን የደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ አስታወቀ። ፓርኩ ባለፉት ስድስት ወራት ከሦስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ማግኘቱን ገልጿል።

የፓርኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ የሺጥላ ሙሉጌታ በፓርኩ ጉብኝት ላደረጉ የጋዜጠኞች ቡድን እንደተናገሩት፤ ፓርኩ ከተተኪ ምርት ዘጠኝ ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከ21 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ አግኝቷል። አፈጻጸሙም ከዕቅዱ አንጻር 225 ነጥብ 7 በመቶ ሆኗል።

ከተተኪ ምርቶች ባለፈ ፓርኩ በስድስት ወራት ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች ከሦስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱንም ጠቁመዋል።

የደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ አምስት ሺህ አምስት መቶ ካሬ ሜትር ስፋት ያላቸው ስምንት ሼዶች እንዳሉት የገለጹት አቶ የሺጥላ፤ ስምንቱ ሼዶች በመንግሥት የተገነቡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪም ፓርኩ ውስጥ 15 ሄክታር መሬት ላይ በግል ባለሀብት የተገነባ የብቅል ፋብሪካ ይገኛል። ፋብሪካው በዓመት 60 ሺ ቶን ብቅል የማምረት አቅም አለው። ፋብሪካው ለአገር ውስጥ ቢራ መጭመቂያ ፋብሪካዎች ግብዓት የሆነውን ብቅል በማምረት ለውጭ ምንዛሬ ይውል የነበረውን ሀብት በማዳን ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ተናግረዋል።

ፓርኩ ውስጥ የተገነቡት ሁሉም ሼዶች በባለሀብቶች መያዛቸውንም የተናገሩት አቶ የሺጥላ፤ በፓርኩ ውስጥ



ፎቶ፡- ናኦል አየለ

ለባለሀብቶች ክፍት የሆነና የሚለማ ተጨማሪ አስር ሄክታር መሬት መኖሩን አስታውቀዋል።

በሚለማው ቦታ ላይ በተለይ በአግሮ ፕሮሰሲንግ እንዲሁም በጨርቃጨርቅ ዘርፍ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ መጥተው መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ አቶ የሺጥላ ከሆነ፤ የደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ በ100 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ የውጭ ምንዛሪ በማስገባት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራና በዕውቀት ሽግግር ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል።

በዚህ ረገድ ባለፉት ስድስት ወራት በፓርኩ ለ687 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን የተገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ በአሁኑ ሰዓት በፓርኩ አንድ ሺ 732 ሠራተኞች ይገኛሉ ብለዋል።

በዕውቀት ሽግግርም ከማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ዘርፎች አንጻር ያሉ ቴክኖሎጂዎችንና ማሽኖችን አጠቃቀም በማስተዋወቅ ረገድ የፓርኩ መገንባት ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው። በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች የተለያዩ ሙያዊ ክህሎቶችን በመቅሰም ዕውቀታቸውንም እያዳበሩበት ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

የፓርኩን ውጤታማነት ይበልጥ ለማሳደግ ግን ችግሮች መኖራቸውን የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ፤ በተለይ ከደብረ ብርሃን ከተማ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ የሚወስደው የአምስት ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር መንገድ ባለመሠራቱ በፓርኩ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ እንቅፋት መፍጠሩን አስታውቀዋል። በመንገዱ ግንባታ ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

# ‹‹መንግሥት ከጨለማ አውጥቶ የእናት አገራችንን አየር እንድንተነፍስ አድርጎናል››

## -ከሳውዲአረቢያ ወደ አገራቸው የተመለሱ ዜጎች

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ከጨለማ አውጥቶ የእናት አገራችንን አየር እንድንተነፍስ ስላደረገን እናመሰግናል ሲሉ ከሳውዲአረቢያ ወደ አገራቸው የተመለሱ ዜጎች አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተናገሩ።

ከስደት ተመላሾቹ እንደተናገሩት፣ ወደ ሳውዲ ለመሄድ የሚያስቡ ወገኖቻችን በእኛ የደረሰ እንዲደርስባቸው አንፈልግም፣ ሞትና እንግልት እንጂ ሌላ ትርፍ የለውም ብለዋል።

በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሳወዲአረቢያ በመሄድ ለአራት አመታት የቆቸው ወይዘሮ ገነት መንግሥቱ ነፍሰጡር ሆና በሳውዲ መንግሥት ተይዛ ለአምስት ወር በአስር ቆይታለች። በእስር ቤት እንዳለች ሴት ልጅ እንደተገላገለች ገልጻ፤ እስር ቤት እንኳን ለነፍሰጡርና ለሕፃናት ለአዋቂ ወንዶች እንኳን ከባድ ነው ብላለች።

ከስደት ተመላሿ እንደገለጸቻው፤ በእስር ቤት ውስጥ እንኳን ለመውለድ ለመጸዳዳትም ከባድ ነው። ‹‹ብዙ እናቶች እስር ቤት እንዳሉ ሕይወታቸው አልፏል፤ እኔ ግን ፈጣሪ ረድቶኝ ወልጄ በሰላም ወደ አገር ቤት ተመልሻለሁ››፤ ለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥትና ፈጣሪን አመሰግናለሁ ብላለች።

በሰላም መመለሳችን ትልቅ ዕድል ነው፣ እኛ ያገኘውን ዕድል ሳያገኙ በእስር ቤት ውስጥ ተሰቃይተው ሕይወታቸውን ያጡ በርካቶች ናቸው ያለችው ወይዘሮ ገነት፤ ባሌን ጨምሮ አሁንም በርካታ ዜጎች በስቃይ ውስጥ ናቸው። መንግሥት እኛን እንደታደገን ሁሉ እነሱንም እንደሚታደጋቸው ተስፋ አለኝ ስትል አስተያየቷን ገልጻለች።

ሌላኛዋ ከስደት ተመላሽ የሆነችው ወይዘሮ አሚና አህመድ በሳውዲአረቢያ ለስድስት አመት ያህል እንደኖረችና የሁለት አመት ሴት ልጇን ይዛ ባላወቀችው መንገድ ለአምስት ወር ያህል ታስራ ሰቆቃና እንግልት እንደደረሰባት ገልጻለች።



ወይዘሮ ገነት መንግሥቱ


ወይዘሮ አሚና አህመድ


ወይዘሮ ነፊሳ መሃመድ

‹‹በእስር ቤት ለሴቶችና ለልጆች የንጽህና መገልገያና የዕለት ምግብ ማግኘት አይቻልም ነበር። እስር ቤት ሕፃን ልጅ ይዞ መታሰር እጅግ ከባድ ነው። በአንድ እስር ቤት ውስጥ ከሁለት መቶ እስከ ሦስት መቶ ሆነን ነው የምንታሰረው። አየር በማይገኝበት ሁኔታ ውስጥ ጨቅላ ሕፃናትን ይዞ መታሰር ሰቆቃው ቃላት የሚገጸው አይደለም›› ብላለች።

በከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ በሚፈራረቅባት ሳውዲ ምቹ ባልሆነበት ሁኔታ እንኳን አምሥት ወር አንድ ቀን መታሰርም ከባድ ነው። በሳውዲ እንደሌሎች አገራት ዜጎች እኩል ክብር አልሰጡንም፤ የታሰርነውም ኢትዮጵያውያን ብቻችንን ነው።

እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ሳውዲ ስቃይ፣ እንግልትና ሞት መኖሩን ሊያውቁ ይገባል። አሁን ላይ በሳውዲ ሕጋዊም ሆኑ ሕገ ወጥ ለኢትዮጵያውያን ያላቸው እይታ እኩል ሆኗል። ሞትና እንግልት በእኛ ይብቃ ያለችው አሚና፤ በየጊዜው ንጽህናቸው እንዲጠበቅላቸው የሚፈልጉ ሕፃናትን ይዞ መታሰር ከፍተኛ ህመም ይፈጥራል ስትል ተናግራለች።

በሳውዲ ለዘጠኝ አመት እንደኖረች የገለጸችው ወይዘሮ ነፊሳ መሃመድ ሁለት ልጆችን ወልዳ ስትኖር ቆይታ ትኬት ቆርጣ ወደ አገር ቤት ልትመለስ ስትል ባልጠበቀችው መንገድ እስር ቤት እንደገባች ትናግራለች። ‹‹ሕጋዊ ሆኜ ስኖር ነበር። ባላወኩትና ባልገባኝ ሁኔታ እስር ቤት ሁለት ልጆቼን ይዤ ታስሬ ከሞት ተርፌ ለእናት አገሬ በቅቻለሁ››። ስትል አስተያየቷን ገልጻለች።

አገራችን ጥሩ አየር ያላትና ለኑሮ ምቹ ናት። ይህን እኛ ኢትዮጵያውያን መለያየትና ጥላቻን በማቆም በአንድነት መኖር አለብን። መንግሥት እኛን አክብሮ ወደ አገራችን መልሶናል እናም መንግሥታችን ማክበርና ማመስገን አለብን ስትል ነፊሳ መሃመድ ገልጻለች።

# ‹‹የላዳ ታክሲዎችን በዘመናዊ መኪናች ለመተካት ቃል ቢገባም ተፈጻሚ አልሆነም››

## -የላዳ ታክሲ አሽከርካሪዎች

# ‹‹ችግሩ የተፈጠረው መኪናቹን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት የሚያስችል አሠራር ባለመኖሩ ነው››

## -የአ.አ.ትራንስፖርት ቢሮ

ኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- የላዳ ታክሲዎችን በዘመናዊ መኪኖች ለመተካት ቃል ከተገባ ከሦስት አመት በላይ ቢያስቆጥርም እስካሁን የተገባላቸው ቃል እንዳልተፈጸመላቸው የላዳ ታክሲ አሽከርካሪዎች ተናገሩ። የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ በበኩሉ የአሽከርካሪዎቹ ቅሬታ አግባብነት ያለው በመሆኑ በጥቂት ቀናት ውስጥ ጥያቄያቸው መልስ ያገኛል ብሏል።



በመገናኛና በፒያሳ አገልግሎት ሲሰጡ ያገኘናቸው የላዳ ታክሲ አሽከርካሪዎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ የከተማዋን የትራንስፖርት መዘመን ጋር ተያይዞ ሌሎቹ የትራንስፖርት ዘርፎች እራሳቸውን እያዘመኑ ሲመጡ ላዳዎች ግን ከዘመኑ ጋር መሻሻል ሳይችሉ ቆይተዋል። ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የላዳ ታክሲዎችን በዘመናዊ መኪኖች ለመተካት ከሦስት ዓመታት በፊት ቃል ቢገባም እስካሁን ወደ ውጤት የተቀየረ ነገር የለም።

ቃሊቲ አካባቢ የሚገኘው የቶታል ሚዛን ሜትር ታክሲ ማኀበር ሥራ አስኪያጅ አቶ ዘሩባቤል መለሰ፣ የከተማዋን ትራንስፖርት የሚያዘምንና አሽከርካሪውንና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግና ለዘመናት ያገለገሉትን የላዳ ታክሲዎች ወደ ዘመናዊ ትራንስፖርት ለመቀየር በአስተዳደሩ በኩል ቃል ቢገባም እስካሁን ጠብ ያለነገር የለም።

ከሦስት አመታት በፊት በከተማዋ አስተዳደር የተጀመረው የላዳ ታክሲዎችን በዘመናዊ ተሽከርካሪዎች የመለወጥ ሂደት በርካታ የላዳ ታክሲ አሽከርካሪዎችን ያስደሰተ ውሳኔ እንደነበር ውሳኔው ለውጤት ሳይበቃ አሳማኝ ባልሆኑ ምክንያቶችና የቢሮክራሲ ማነቆዎች ሂደቱ ተወላክፎ እንደቀረ አቶ ዘሩባቤል ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዘሩባቤል ገለጻ ማህበራቸው 70 አባላት ያሉት ሲሆን በየግለሰቡ ምርጫ 650 ሺህ እና 570 ሺህ ዋጋ ላላቸው መኪኖች 20 በመቶ ቅድመ ክፍያ ለኤል አውቶ አስመጪ ድርጅት ከተከፈለ አንድ ዓመት ሆኖታል። ኩባንያውም ከቀረጥ ነፃ መብት በመንግሥት ስላልተሰጠው መኪኖቹን ማስመጣት አልቻለም።

በመገናኛ አካባቢ የሚገኘው የውብ ሜትር ታክሲ ማኀበር አባልና የላዳ ታክሲ ሹፌር አቶ ጌትነት ተክለሃይማኖት በበኩላቸው፣ ራይድ የመሳሰሉት ዘመናዊ ታክሲዎች ከመጡ በኋላ እየተቀዛቀዘ የመጣውን የላዳ አገልግሎት በዘመናዊ መኪኖች ለመቀየር አስፈላጊውን ክፍያ ከከፈሉ አንድ ዓመት እንደሆናቸው ገልጸዋል።

ሰባት ሰው የሚይዘውን አዲሱን ዘመናዊ መኪና መርጠው ከጠቅላላ 650 ሺህ ብር 20 በመቶውን 130 ሺህ ብር ለአስመጪ ኩባንያው ከፍለው እየተጠባበቁ መሆኑን ገልጸዋል።

የላዳ ሥራ እየተቀዛቀዘ የመጣ በመሆኑ ቀኑን ሙሉ ሥራ እየተሠራ ባለመሆኑ ቤተሰብ ለማስተዳደር መቸገራቸውን ገልጸው፣ በከተማ አስተዳደሩ የተገባው ቃል በፍጥነት እንዲጀመር ጠይቀዋል።

አስመጪ ኩባንያውና መንግሥት አስፈላጊውን ስምምነት በመፈጸም የተገባው ቃል ወደ ተግባር በአፋጣኝ ተግባራዊ በማድረግ መፍትሄ ቢሰጡ ሲሉም ጠይቀዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አረጋዊ ማሩ በበኩላቸው እንደተናገሩት፣ በከተማዋ የሚገኙት 10 ሺህ 100 አባላት ያሉት 185 የላዳ ታክሲ ማኀበራት ላለፉት 50 ዓመታት በላይ በትራንስፖርቱ ዘርፍ የማይተካ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል።

የከተማ አስተዳደሩም ላዳዎቹን በአዲስ ለመተካትና የላዳ መኪኖችን ውለታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ለማዘመን ትኩረት አድርጎ እየሠራ ነው።

ለረጅም አመታት ሲያገለግሉ የቆዩትን የላዳ ታክሲዎች በአዳዲስ ዘመናዊ መኪኖች ለመተካት በተደረሰው ስምምነት መሠረት ወደ ሥራ መግባት የሚጠበቅ ቢሆንም መኪኖቹን ቀረጥ ከፍሎ ማስገባት የሚያስችል አቅም ባለመኖሩ የትራንስፖርት ቢሮው ኃላፊነቱን ወስዶ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የማመቻቸት ሥራ ማስጀመሩን አስታውሰዋል።

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ በማኀበራቱና እና በአቅራቢ ድርጅቶች መካከል ውል እንዲፈፀም በማመቻቸት በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገባ ጥረት ሲያደርግ ነበር ያሉ ሲሆን አሁን የቀናት ጉዳይ ብቻ ይቀራል ብለዋል።

‹‹እስካሁንም ወደ ሥራ እንዳይገባ ምክንያት የሆነው ሚኒስትሮች ምክር/ቤት የሚያወጣውን ደንብ ተከትሎ መኪኖቹን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት የሚያስችል መመሪያውን አውጥቶ ማጸደቅ ግድ ስለሚል ነው። አሁን መመሪያውን የማጽደቅ ሥራ እየተሠራ ነው። መመሪያው ሲፀድቅ የላዳ አሽከርካሪዎች ጥያቄ መልስ ያገኛል›› ብለዋል። የላዳ ታክሲ ማኀበራትም ከቀረጥ ነፃ መመሪያው እስኪጸድቅ በትዕግስት እንዲጠብቁ አሳስበዋል።

ከቀረጥ ነፃ ከሚገቡት ዘመናዊ መኪኖች ባሻገርም ኤል አውቶ የተሰኘ ድርጅት የተወሰኑ መኪኖቹን አምርቶ ለማስረከብ በዝግጅት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ኤች.አር 6600 እና ኤስ 3199 ረቂቅ ሕጎችን ለማስቆም የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግሥት ጥሪ አቀረበ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ ኮንግረንስ የሚቀነቀንላቸው ኤች.አር 6600 እና ኤስ 3199 ረቂቅ ሕጎችን ፅድቀት ለማስቆም በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥሪ አቅርቧል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለፁት፣ ኤች አር 6600 እና ኤስ 3199 ይዘታቸው በአገርም በሕዝብም ላይ ጫና የሚፈጥሩ ረቂቆች ናቸው። በመሆኑም የረቂቅ ሕጎችን ፅድቀት ለማስቆም በሳንፍራንሲስኮ፣ በዋሽንግተንና በሌሎችም የአሜሪካ ከተሞች የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባ ነው።

ረቂቅ ሕጎቹ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የሆነ ሁለገብ ጫና የሚፈጥሩ በመሆናቸው እነዚህ ጫናዎች ሕዝብንም አገርንም ይጎዳሉ ብለዋል አምባሳደሩ።

ስለሆነም መንግሥት በተለያዩ ተቋማቱ ከሚሠራው ዲፕሎማሲያዊ ሥራ በተጨማሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንደ አገር ይህ ማዕቀብ ከተጣለ የሚያደርሰውን ችግር በመረዳት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ ነው። ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ተግባር ነው።

ከዚህ በፊት በተካሄዱ እንቅስቃሴዎች ከአገር ውጭ በተለያዩ አካባቢዎች ሰላማዊ ሰልፎችና የፊርማ ማሰባሰብ ሥራዎች እየተካሄዱ ነው። የተለያዩ የሴኔት አባላትን በማግኘትም እነሱ ላይ ተፅዕኖ የማሳረፍ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል አምባሳደር ዲና።

ረቂቆቹን የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች ማንቀሳቀሱን እንደቀጠሉ ስለሆነና በየደረጃው እስከመጨረሻው ይህንን ያስቀጥላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጥረት ይህ ረቂቅ አስፈላጊ አለመሆኑን ተረድተው እስኪተውት ድረስ ትግሉ መቀጠል ይኖርበታል ብለዋል።

በዚህ ሰዓት ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ ለመጣል የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች የሉም ያሉት አምባሳደሩ መንግሥት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግሥት ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማድረግ በቂ ጥረት እያደረገ መሆኑና በአገር ደረጃ ሰላማዊ ምክክር ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ኮሚሽን በተመሠረተበት ሁኔታ ረቂቅ ሕጎችን በሰብዓዊ መብት ሕግ ጥሰት ሥም ለማፅደቅ መጣደፍ ተገቢ አለመሆኑን አመላክተዋል።

ከዚህም ባለፈ የተወሰኑ የፖለቲካ እስረኞች በተፈቱበት እና ከሁሉ በላይ ደግሞ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ያለውን ግጭት ላለማስፋፋት መንግሥት ጥልቅ ትዕግስቱን ባሳየበት ሁኔታ እና የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እየተሠሩ ባሉበት ሁኔታ ይህን ማዕቀብ ለመጣል የሚያነሳሳ ምክንያት የለም ብለዋል አምባሳደሩ።

መንግሥት እያከናወናቸው ካሉ ተግባራት አኳያ የረቂቅ ሕጎቹ በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የሚኖረውንም ግንኙነት ይጎዳሉ። የሁለቱንም አገራት ታሪካዊ ግንኙነት የሚመጥንም አይደለም። በአጠቃላይ በአገር ውስጥ የተጀመረውን የሰላም ጥረት የሚያደናቅፍ ነው።

# መንግሥት በሳውዲአረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ 100ሺ ዜጎችን መመለስ ጀመረ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በሳውዲአረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ መቶ ሺህ የሚሆኑ ዜጎችን ወደ አገር ቤት መመለስ መጀመሩን ገለጸ። የሚመለሱ ዜጎችን በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ይደረጋል ተብሏል።

ዜጎችን የመመለስ ሥራውን ትናንት አራት መቶ የሚሆኑ ዜጎችን በመቀበል መጀመሩን የገለጹት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ እንደገለጹት፤ በሳውዲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የመመለስ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሰፊ የዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ሥራ ተሠርቷል።

በገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴና በብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የተመራ የደህንነትና የጸጥታ አካላትን ያካተተ በሁለት ዙር የልዑካን ቡድን ወደሳውዲ በማቅናት ከሳውዲአረቢያ መንግሥት ጋር የዲፕሎማሲ ሥራ ሠርቶ መመለሱን ገልጸዋል። ይህም ዜጎችን በአግባቡ ክብራቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ሁኔታ ላይ ውይይት በማድረግ በምን ሁኔታ እንደሚመለሱ ስምምነት ላይ ተደርሶ የተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ብርቱካን ገለጻ፤ ዜጎችን ወደ አገር ቤት ለመመለስ ባለፈው የካቲት 15 ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ዜጎችን ለመመለስ ለተቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ በሰጡት አቅጣጫ መሠረት ዝግጅት ተደርጎ ስደተኞችን መመለስ መጀመሩን ገልጸዋል።

ተመላሾቹ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ ቢሆንም አብዛኞዎቹ ከአማራና የኦሮሚያ ክልል ናቸው ያሉት አምባሳደሯ፤ አስፈላጊው ቁሳቁስ፣ አልባሳትና የመሳሰሉት ጊዜያዊ መቋቋሚያ የሚያስፈልጋቸው ተለይተው ድጋፍ ከተደረገላቸው በኋላ ወደየመጡበት አካባቢ በመመለስ በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ይደረጋል። ዜጎችን ለማቋቋም በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስፈላጊውን ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰዋል። ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ ወደ የመጡበት አካባቢ ሄደው እንዲቋቋሙ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ስደተኞቹ በቀን በሦስት በረራ ወደ አገር ቤት የሚመለሱ ሲሆን በቅድሚያ ሴቶችንና ሕፃናትን እንዲመለሱ ይደረጋል። በቀጣይም አረጋውያንና ወንዶችን የመመለስ ሥራ እንደሚሠራ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ ገልጸዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶክተር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ዜጎችን የመመለስ ሥራ ከሳውዲ መንግሥት ጋር ሰፊ ውይይቶችን የጠየቀና ረጅም ጊዜ የወሰደ ሥራ ነው። የሚመለሱ ዜጎችን የልየታ ሥራ መሥራትና ከተመለሱ በኋላ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ የመሥራት ሂደት ረጅም ጊዜ የወሰደ ነው።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ተመላሾቹ ከጊዜያዊ ማረፊያ የቦታ ዝግጅት ጀምሮ በቀጣይ ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው በዘላቂነት እንዲቋቋሙ የማድረግ ተግባር ከተለያዩ ተቋማትና ሴክተር መስሪያ ቤቶች በቅንጅት እየተሠራ ነው።

መንግሥት ዜጋ ተኮር የዲፕሎማሲ ሥራ ከመሥራት አንጻር ከዚህ በፊትም በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዜጎች ተመላሽ እንደሆኑ ያስታወሱት ኤርጎጌ (ዶክተር)፤ መቶ ሺህ ዜጎችን የመመለስና መልሶ የማቋቋም ሥራው ሰፊ ሥራን የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

በዘላቂነት እንዲቋቋሙ የማድረጉን ተግባር ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን እየመራ የሚሠራ ሲሆን 16 የሚደርሱ ተባባሪ ተቋማት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ በቅንጅት እየተሠራ ነው ተብሏል።

# የፈርኒቸር የቤተ ውበትና የግንባታ አጨራረስ አውደ ርእይ ሊከፈት ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ለተሳታፊዎች ዘላቂ የንግድ ትስስርን ይፈጥራል የተባለለት የፈርኒቸር የቤተ ውበትና የግንባታ አጨራረስ "FINTEX" ዓለም አቀፍ አውደርእይና ጉባኤ ሊካሄድ መሆኑ ተገለፀ።

ጉዳዩን በሚመለከት በትናንትናው ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት የአውደ ርእዩ አዘጋጅ አክሊሉ በለጠ እንደገለፁት፤ ዝግጅቱ በአገራችን ያሉ የፈርኒቸር የቤተ ውበትና የግንባታ አጨራረስ ኢንዱስትሪ ዘርፍን ተገቢውን እውቅና ለመስጠትና ለመደገፍ ታቅዶ የሚዘጋጅ ነው።

ፊንቴክስ አውደ-ርዕይ ላይ የአገር ውስጥ አምራቾችን እና ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን በአንድ ጣርያ ስር በማሰባሰብ መንግሥትን ከንግዱ ማኅበረሰብ እንደሚያገናኝ አቶ አክሊሉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለፃ መድረኩ ከዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ፣ ከበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በመገንባት ላይ ከሚገኙ ባንኮች፣ ሆስፒታሎች፣ጤና ጣቢያዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የንግድ ማዕከላት፣ ሲኒማ ቤቶች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ከአነስተኛና ጥቃቅን በማደግ ላይ ለሚገኙ የፈርኒቸር አምራቾችም ዕድል ይፈጥራል።

ሁነቱን የሚያስተባብረው የፕራና ኢቨንትስ መስራችና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ነብዩ ለማ በበኩላቸው የቤተ ውበትና የግንባታ አጨራረስ አውደ ርዕይ ዘርፉን ከማበረታታት አንፃር የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል።

እንደ አቶ ነብዩ ገለፃ፤ መድረኩ በኢንዱስትሪ ዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎች የደረሱበትን የቴክኖሎጂና የምርት የእድገት ስኬት ደረጃ፣ ልምድና ተሞክሮ የሚያካፍሉበት፤ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ጥናታዊ ጽሑፍ የሚያቀርቡበት ነው።

አውደርእዩ በኢንዱስትሪ መስኩ የተሰማሩ እና ለመሰማራት በጥናት ላይ የሚገኙ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ከሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ስለ ኢንዱስትሪው ተግዳሮቶችና ቀጣይ የእድገት አቅጣጫ እና የመንግሥት ስትራቴጂ ገለጻና የፓናል ውይይት የሚደረግበት መድረክ መሆኑንም አብራርተዋል።

በአገራችን መጠነ ሰፊ የመሠረተ ልማት እና ልዩ ልዩ ግንባታዎች ማደግና ማኅበረሰባችን ወደ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ በፍጥነት መግባት ጋር ተያይዞ የገበያው ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ ማደጉን የጠቆሙት አቶ ነብዩ ሁኔታው ለፈርኒቸር፣ ለቤተ-ውበት እና የግንባታ አጨራረስ ዘርፎች የፈጠራ ሥራ መጨመር እና እድገት መንገድ መከፈቱንም ተናግረዋል።

FINTEX አውደርዕይና ጉባኤ ለሦስተኛ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን የዘንድሮው «ንግድዎን በመቅረዝ ላይ ያኑሩ» በሚል መሪ ቃል እንደሚካሄድና ከአገር ውስጥ እንዲሁም ከውጭ የሚመጡ ከ 60 በላይ ኩባንያዎች ተሳታፊ እንደሚሆኑ በጋዜጣዊ መግለጫው ተመላክቷል።

# የሽብር ቡድኑ በበራህሌ፤...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መግባት ይችላሉ ያሉት አቶ አብዱ፤ ለዚህም መላው የአፋር ሕዝብና መንግሥት በቀናነት ትብብር እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

የአፋር ክልል የብልጽግና ፓርቲ አፋር ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ መሐመድ ሁሴን በበኩላቸው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአፋር ክልል ወረራ በመፈፀም አምስት ወረዳዎችንና አንድ የከተማ አስተዳደርን ይዟል ብለዋል።

በወረራው 600 ሺህ ሰዎች ከአፋር ክልል የተፈናቀሉ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ በተለይ ከዞን ሁለት 480 ሺህ ሰዎች መፈናቀላቸውን ገልጸዋል።

የአፋር ሕዝብ በሽብር ቡድን የተነሳ ጉዳት እየደረሰበት ቢሆንም የትግራይ ሕዝብም እንደኛው ችግር ውስጥ ያለ ኢትዮጵያዊ ነው በሚል ስሜት የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅራቢ ተሽከርካሪዎች እንዲያልፉ ትብብር እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ይሁንና አሸባሪው ሕወሓት በአብዓላና በተለያዩ የአፋር አካባቢዎች በከፈተው ጦርነት የተነሳ ተሽከርካሪዎች ወደትግራይ ክልል ገብተው የጫኑትን ዕርዳታ ማድረስ አልቻሉም ብለዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በበኩሉ የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት በተመለከተ ከትናንትና በስቲያ መግለጫ አውጥቷል።

በወቅቱ የአብኣላ የዕርዳታ ማስተላለፊያ መንገድ በሕወሓት ታጣቂዎች በመዘጋቱ የተነሳ 43 የጭነት መኪና የዕርዳታ ዕህል የጫኑ ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ ክልል ሊገቡ እንዳልቻሉ ገልጿል።

በተለይም 20 የጭነት መኪናዎች የዕርዳታ እህሉን እንደጫኑ በአፋር ክልል በሠመራ ከተማ መቆማቸውንም መንግሥት አስታውቋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል ሰብአዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦቱን ለማሳለጥና በከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ለመታደግ ለሰብዓዊነት ሲባል ግጭት መቆሙን ማስታወቁ የሚታወስ ነው።

ውሳኔው ከተወሰነበት ቀን አንስቶ የተለያዩ ዕርምጃዎች እየተወሰዱ ሲሆን፤ በተለይ በሳምንት ሁለት ጊዜ ይደረግ የነበረውን የሰብዓዊ ድጋፍ የአየር በረራ በየቀኑ እንዲደረግ ለተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ ርዳታ አቅራቢ ተቋማት ፍቃድ መስጠቱን መንግሥት አስታውቋል።

በዚህም መሠረት ረጂ ድርጅቶች በቻሉት መጠን የመድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ ገንዘብና አልሚ ምግቦችን በአየር ትራንስፖርት ማጓጓዝ መጀመራቸው ተገልጿል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል ያሉ ዜጎችን ለመታደግ ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም ዕርዳታውን ለማቅረብ እንቅስቃሴ ውስጥ የገባ ቢሆንም የሌላኛውን ወገን ቅን ትብብር ማግኘት እንዳልቻለ አስታውቋል።

የትግራይ ታጣቂዎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከመደርደርና የተዛቡ መረጃዎችን ከማሠራጨት ተቆጥበው የዕርዳታ ዕህሉን አቅርቦት ማሳለጥ እንዳለባቸው መንግሥት አሳስቧል።

በዚህ ካለፈ በወረራ ከያዙዋቸው የአፋርና የአማራ ክልል ወረዳዎች በመውጣት ግጭት ለማቆም የገቡትን ቃል እንዲያከብሩ የዓለም አቀፍ ተቋማት በትግራይ ታጣቂዎች ላይ ጫና እንዲያደርጉ መንግሥት ጥሪ ማቅረቡ የሚታወስ ነው።

# ለዘንድሮ የችግኝ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መሆኑን አስታውሰው በዚህ ዓመት የአየር ንብረት ለውጥ እና በሌሎች አገራዊ ምክንያቶች የተወሰነ ቢቀንስም በርካታ ቁጥር በመተከሉ የጽድቀት መጠኑ ጥሩ የሚባል እንደሆነ ጠቁመዋል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት 20 ቢሊዮን ችግኞች በአራት አመት ለመትከል ዕቅድ ተይዞ የተጀመረ ሲሆን፣ በዘንድሮ ክረምት ይህ የመጀመሪያው ዕቅድ ይጠናቀቃል። በሦስት አመት ውስጥም ከ17ቢሊዮን ችግኝ በላይ መተከሉን አስታውሰው ዘንድሮ ከሚተከለው ጋር ከእቅዱ በላይ ማሳካት እንደሚቻል ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

አቶ ኡመር እንደሚናገሩት፣ የችግኝ ተከላው የሚቆም ሳይሆን በሁለተኛው ሳይክል የሚቀጥል ነው። በሁለተኛዉ ሳይክል ጥራትን መሠረት በማድረግ ለምግብነት የሚውሉ እና የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ እና ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን ሊተኩ በሚችሉ ችግኞች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

ከጎረቤት አገራት ጋር ትብብር ለመፍጠር እና በሕዝቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ታስቦ በተያዘው እቅድም ወደ ጅቡቲ ችግኝ ተልኮ ተተክሏል። ለኤርትራእና ደቡብ ሱዳንም በተቻለ መጠን በአውሮፕላን እና በመኪና ችግኞች መላክ ተችሏል። በቀጣይም ዓለም ላይ የተጋረጠውን የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና በጋራ ለመልማት ኢትዮጵያ የምታደርገው ድጋፍ እየተጠናከረ እንደሚሄድ የገለጹት ሚኒስትሩ አሁን ጅማሬው መልካም መሆኑን ተናግረዋል።

የዘንድሮ 2014ዓ.ም ክረምት የችግኝ ተከላ የሚጀመርበት ጊዜ በእርጥበት ምጣኔ የሚወሰን ነው ያሉት ሚኒስትሩ እንደሚኖረው እርጥበት ሰኔ ውስጥ ወይም ሐምሌ የመጀመሪያ ሳምንታት ውስጥ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል። ኅብረተሰቡም ለችግኝ ተከላው ጥሪ ሲደረግ በተለመደው መልኩ በነቂስ ወጥቶ በመትከል አገራዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስሰላም የተዘረጉትን የኢትዮጵያ እጆች የረገጡት ተገቢ ያልሆኑ ረቂቅ ሕጎች!

አገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያዩ ዓለምአቀፍ ጫናዎችን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች። በአንድ በኩል በአሸባሪው ሕወሓት አማካኝነት የተከፈተባትን ጦርነት ለመመከት እየወሰደች ያለውን እርምጃ ለማደናቀፍ የሚደረጉ የውጭ ጫናዎች፤ በሌላ በኩል ደግሞ የታላቁ ህዳሴ ግድብን ከጫፍ ለማድረስ መስራቷን ተከትሎ ይህንን ለማስቆም የሚደረጉ ጫናዎች በርካታ ፈተናዎችን አስተናግዳለች፣ እያስተናገደችም ትገኛለች፡፡

በዚህ ረገድ ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ ብቻ በፀጥታው ምክር ቤት 13 ጊዜ በኢትዮጵያ ጉዳይ በመሰብሰብ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር ተሞክሯል። ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያን ለማፍረስ በቅንጅት የሚሠሩት አንዳንድ ምዕራባውያን ሚዲያዎች የሃሰት ዘገባዎችን ጭምር በመፈብረክ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር ያልፈነቀሉት ድንጋይ፤ ያልማሱት ጉድጓድ የለም። በተለይ አሸባሪውን ሕወሓት ከቀብር በማስነሳት እንደ አዲስ ሕይወት እንዲዘራ ከማድረግ ጀምሮ ቡድኑ አዲስ አበባ ሊገባ እንደሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመዘገብና የኅብረተሰቡን ስነልቦና በመስለብ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከፍተኛ ሙከራ አድርገዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ስም የያዙና በግብረሰናይ ስም የተቋቋሙ ድርጅቶችና ተቋማት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ከተቋቋሙለት ዓላማ ውጪ ሲሠሩም ሰንብተዋል። ከዚህ አንጻር ዓለምአቀፉ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን አምነስቲ ኢንተርናሽናል፤ በሕወሓቱ ቀንደኛ ሰው ዶክተር ቴዎድሮስ አድሃኖም የሚመራው የዓለም ጤና ድርጅት፤ የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት እና የመሳሰሉ ተቋማት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ኢትዮጵያን ለማንበርከክ ከፍተኛ ደባ ሲፈጽሙ ሰንብተዋል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን የአሜሪካ ኮንግረስና ጥቂት ከሕወሓት ጋር እጅና ጓንት የሆኑ ባለስልጣኖቻቸው በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ ቆይተዋል። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያና በሕዝቦቿ ላይ ጫና ለማሳደር የሚያደርጉትን ሴራ ዛሬም በተጠናከረ ሁኔታ ቀጥለውበታል። በኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ የእንቅስቃሴ ገደብ በመጣል የተጀመረው ጫና ቀስ በቀስ ምህዳሩን በማስፋት በሕዝቦቿ ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ሲፈፅም ቆይቷል። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያን ከአጎዋ ተጠቃሚነት ማገድ አንዱ እርምጃ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ ኤችአር 6600 እና ኤስ 3199 የተሰኙ ረቂቅ ሕጎችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ በኢትዮጵያ ላይ የጀመሩትን ጫና በተጠናከረ ሁኔታ ቀጥለውበታል። እነዚህ የሰሞኑ ሕጎች በዋናነት ከላይ ሲታዩ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ጦርነት መነሻ በማድረግ ሰላም ለማምጣት ያለሙ በመምሰል የቀረቡ ናቸው። በዚህም መሠረት ሕጎቹ የኢትዮጵያ የመረጋጋት፣ የሰላም እና የዴሞክራሲ ሕግ (Ethiopia Stabilization, Peace, and Democracy Act) በሚል ስያሜ ቀርበዋል። ነገር ግን የማዕቀቦቹ ዋነኛ የትኩረት መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ነው። በዚህም መሠረት እነዚህ ረቂቅ ሕጎች ሙሉ በሙሉ ፀድቀው ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለማስከተል ታስቦ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

አንዳንድ የዘርፉ ምሁራን እንደሚሉት የአሜሪካ ኮንግረስ አባላት በሕጎች ላይ ያላካተቱት ነገር ቢኖር፣ «የመንግሥትን ስልጣን ለሕወሓትና ሸኔ አስረክቡ የሚለው ዓረፍተነገር ብቻ ነው» ሲሉ ተደምጠዋል። «የኢትዮጵያን ህልውናና ነፃነት የሚዳፈር ብቻ ሳይሆን ማዕከላዊው መንግሥት እንዲዳከምና ኢትዮጵያ የሊቢያን መንገድ እንድትከተል ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ አደገኛ ሕግ ነውም» ይሉታል፡፡

አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምታደርገውን የደኅንነትና የንግድ ድጋፍ እንድታቆም እንዲሁም ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ አበዳሪዎችና የገንዘብ ምንጮች (አይኤምኤፍና የዓለም ባንክን ጨምሮ) ገንዘብ እንዳታገኝ እስከ ማድረግ የሚደርስ ዕርምጃም ተካቶበታል፡፡

በኢንቨስትመንት ዘርፍ ደግሞ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ፋይናንስ ኮርፖሬሽኖች ጋር ያላትን ግንኙነት በማገድ ኢንቨስትመንቶችንና የገንዘብ ልውውጦችን የማስቆም ዓላማ አለው። ረቂቅ ሕጉ መሠረታዊ መብቶችንም ያግዳል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎችና አጋሮች በኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዳያደርጉም ሆነ ገንዘብ እንዳይልኩ ይከለክላል። የኢሚግሬሽን ገደቦችንም ያካተተው ይህ ረቂቅ ሕግ የቪዛ አመልካቾችና የወደፊት የዲቪ ማመልከቻዎች መሰረዝንም የሚያካትት ነው።

«ይህ ረቂቅ ሕግ ከጸደቀ የአገሪቱ ኢኮኖሚን በከፍተኛ መልኩ በማድቀቅ በእያንዳንዱ ዜጋ ኑሮ ላይ ከባድ ጫና በማድረስ እጅግ አደገኛ ሁኔታን የሚፈጥር ነው። ከዚህም ባሻገር በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድ ግንባት ዙሪያ የመሠረተ ልማቶች ግንባታን ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ ድጋፎችና ብድሮችን በመከልከል ኢትዮጵያ መሠረተ ልማት ግንባታዋን እንዳታስቀጥል እክል የሚፈጥር ነው፡፡

አሳዛኙ ነገር እንዲህ ያለ ጫና የሚደረገው ኢትዮጵያ ለሰላም እጇን በዘረጋችበትና ለዚሁ ብዙ ዋጋ እየከፈለች ባለበት ጊዜ ላይ መሆኑ ነው። ከሰሞኑ ሰብአዊ ርዳታ ወደትግራይ እንዲደርስ በሚል ግጭት ማቆሙን መንግሥት በይፋ አሳውቋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ እርምጃዎች በመንግሥት ቢወሰዱም ሕጎቹ ግን ተግባራዊ ወደመሆን እየሄዱ ነው። ይህ ደግሞ የሕጎቹ አርቃቂዎች ዋነኛ እቅድ ኢትዮጵያን ማዳከም መሆኑን በግልጽ ያሳያል። በመሆኑም ይህ ሕግ በምክር ቤቱ እንዳይፀድቅ መታገል ለኢትዮጵያ ዘላቂ ዕድገትና ልማት መታገል በመሆኑ ረቂቅ ሕጎቹ እንዳይጸድቁ መላ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ትግላቸውን ዛሬም አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል!


ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ገበያን ማዛባት፣ ሌላኛው የሸብርተኝነት መገለጫ

**ውቤ ከልደታ**

ሰላም ጤና ይስጥልን ውድ የአዲስ ዘመን ቤተሰቦች፤ እንደምን ከረማችሁ? ይህንን ሰላምታ ያቀረብኩት በመጠፋፋታችን ብቻ አይደለም፤ በየሳምንቱ አዳዲስ አጀንዳዎችን ማስተናገድ የዘወትር ባህላችን እየሆነ በመምጣቱ ነው። እድሜ ለቴክኖሎጂ ወለዱ ማህበራዊ ሚዲያ ይሁንና አዳዲስ አጀንዳዎቻችን በየጊዜው መቀያየራቸው አዲስ አይደለም፡፡

አሁን አሁን ሳምንት አልፎ ሳምንት ሲተካ አጀንዳዎቻችን በዚያው ልክ ሲቀያየሩ ማየት እየተለመደ ነው። የአጀንዳዎቻችን ፈጣሪዎች ደግሞ አንድም ማህበራዊ ሚዲያውን የገቢ ምንጭ ያደረጉ የወሬ ነጋዴዎች ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዴ መንግስት፤ ሌላ ጊዜ መንግስት ገሸሽ ያደረጋቸው ስልጣን ፈላጊዎች፤ የአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች አልያም ህብረተሰቡ ራሱ ነው፡፡

ሰሞኑን ጥቂት ሳምንታት ዘለግ ላለ ጊዜ መነጋገሪያ ከነበሩ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛው የኑሮ ውድነት ነው። በተለይ የዘይት ዋጋ መናር ከመነጋገሪያነትም አልፎ የቀልድ ምንጭ ሲሆን ተመልክተናል። ይህ መሰረታዊ የሸቀጥ ምርት በድንገት ተነስቶ ጣሪያ የመንካቱ ምስጢር እስካሁን በግልጽ ባይታወቅም የተለያዩ መላምቶችና ምክንያቶች ሲሰነዘሩ ግን ሰምተናል። ከነዚህም ውስጥ የአምራቾች ጥሬ እቃ ማጣት፣ የሃይል አቅርቦት ችግር፤ የሩስያና ዩክሬን ጦርነት፣ በነጋዴና በሸማች መካከል ያለ ደላላ፤ ወዘተ የመሳሰሉት ምክንያቶች ከተነሱት ነጥቦች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በእኔ እምነት እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይነስም ይብዛ የየራሳቸው ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ነገር ግን ሁሉም ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው የሚል እምነት የለኝም። በተለይ የሩስያና ዩክሬን ጦርነት ለዘይት ዋጋ መናር ምክንያት ነው የሚል እምነት የለኝም።

በቅድሚያ የኔን ገጠመኝ ላንሳ። የዘይት ዋጋ አንድ ሺህ ብር ገባ በሚል መወራት የጀመረው ቅዳሜ እለት ከሰዓት በኋላ ነበር። በእለቱ እንዳጋጣሚ ሆኖ ጠዋት ላይ ለቤታችን የሚያስፈልግ ዘይት ገዝተን ነበር። በእለቱ አምስቱ ሊትር ዘይት የተገዛው በ650 ብር ነበር፡፡

ከዚያ ከሰዓት በኋላ የዘይት ዋጋ አንድ ሺህ ብር መግባቱ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ተጥለቀለቀ። ከዚያ በየመንደሩ የማህበራዊ ሚዲያ የሚጠቀመውም ሆነ የማይጠቀመው ይህን ወሬ በብዙ እጥፍ አባዛው። ለካ የሰፈር ወሬ ከማህበራዊ ሚዲያው በላይ የመስፋፋት አቅሙ ከፍተኛ ነው። ከዚያ ጥቂት ጎረቤቶቻችን በመምጣት ዘይት ከዚህ ሳይብስ ለምን አትገዙም በሚል ግማሹ በምክር መልክ፤ ከፊሉ ደግሞ ካለን ቅርበት የተነሳ በራችንን ማንኳኳት ጀመሩ። ከዚያ እኛ ጠዋት ከገዛንበት ቤት ከሰዓት በኋላ በአንድ ሺህ ብር መቸብቸብ ተጀመረ፡፡

እንግዲህ እነዚህ ነጋዴዎች በ650ም ሆነ በ1000 ብር ሲሸጡ የነበረው ዘይት በተመሳሳይ ዋጋ የተገዛ መሆኑ እሙን ነው። ለዋጋ መጨመር ምክንያት የሆናቸው የገበያው ሁኔታ ሳይሆን ገና ለገና ዘይት ጨምሯል የሚለው ወሬ ነው። እና ከትክክለኛ ዋጋ ይልቅ ወሬ የአገራችንን ዋጋ እየተቆጣጠረ ስለመሆኑ ልብ እንበል፡፡

በዚህ አጋጣሚ ከእነዚህ ስግብግብ ነጋዴዎች ባልተናነሰ የስግብግብ ሸማችም ለዋጋ ንረቱ አስተዋፅኦ እንዳለው ልብ ልንል ይገባል። በአገራችን ገና ለገና አንድ እቃ ከገበያ ይጠፋል በሚል ከዋጋው በላይ ለመግዛት መሯሯጥ የተለመደ ነው። በተለይ «እንዲህ አይነት እቃ ጠፋ፤ ዋጋ ሊጨምር ነው» ከተባለ አብዛኛው ሰው ወዲያው ተበድሮም ቢሆን ከመግዛት አይመለስም። ገና ዋጋ ጨመረ ሲባል ተሰልፎ ለመግዛት ይወጣል። የሚያሳዝነው ደግሞ አንዳንዱ ለማከማቸት እንጂ ለመብላት የሚገዛ እስከማይመስል ድረስ በጅምላ ለመግዛት መሯሯጡ ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ በተለይ በህገወጥ መንገድ ገንዘብ የሚያገኙ ሰዎች በተገኘው ዋጋ በመሸመት ዋጋ ለማናር ዋነኛ ምክንያቶች ይሆናሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት ያጋጠመኝን ላካፍላችሁ። የበዓል ሰሞን ነው። ከዚያ አንድ ወዳጃችን ባለው አቅም በግ ለመግዛት ወደ አዲሱ ገበያ ይሄዳል። እዚያ ሲደርስ ሸማቹ እና ነጋዴው እየተተራመሰ ነው። ይህ ወዳጃችንም ዞር ዞር ብሎ የበግ ዋጋ መጠየቅ ይጀምራል። ከዚያ በአጋጣሚ አንድ ቦታ ላይ የሚፈልገው በግ ያገኛል።

ከዚያ ዋጋ ሲጠይቅ በወቅቱ ዋጋ 2500 ብር እንደሆነ ይነገረዋል። ከዚያ እሱ ዋጋ እንዲቀነስለት፤ ነጋዴው ደግሞ ብዙ ላለመውረድ ወደ ክርክር ይገባሉ። ከዚያ ከ2300 ብር በፍጹም እንደማይቀንስ እየተናገረ እያለ፤ ከነሱ አቅራቢያ አንድ የመንግስት ታርጋ የለጠፈ መኪና ይቆማል። ከዚያ ነጋዴው ከዚህ ቀደምም ያውቃቸው ኖሮ ፈጠን ብሎ ወደነሱ ይሄዳል። ከዚያ ቀደም ብሎ በጉን ለመግዛት ተቃርቦ የነበረው ወዳጃችን ነጋዴውን እንዲሸጥለት ቢጠይቀውም፤ ፊት ነስቶት በቀጥታ ከአዲሶቹ ደንበኞች ጋር ማውራቱን ይቀጥላል፡፡

ከዚያ አዲሶቹ ሸማቾች በአጋጣሚ ወዳጄ ሊገዛ የነበረውን በግ ይዘው ዋጋ ይጠይቃሉ። ከዚያ ነጋዴው ያለምንም ይሉኝታ ሶስት ሺህ ብር ነው ሲል ይመልስላቸዋል። ከዚያ እነሱ አንተ በቃ ሁሌም ዋጋህ አይቀመስም በሚል ከቀለዱ በኋላ ሁለተኛ እንኳ ለመጠየቅ ሳይፈልጉ በል መኪናው ላይ ጫነው በሚል ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ከዚያ ወዳጄ እያየ ሊገዛው የነበረውን በግ ተቀማ። ከዚያ ጥቂት ቆይቶ ሁኔታው ሲጣራ በአንድ ክፍለከተማ የሚሰሩ ኃላፊዎች እንደሆኑ ተገነዘበ።

በእርግጥ እነዚህ ሰዎች ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል የተለየ ገቢ የሚያገኙ አይደለም። ነገር ግን እነሱ ምናልባት በህገወጥ መንገድ የሚያገኙት ገቢ ሊኖር እንደሚችል አሰበ። ይህንን ለማለት ያደረሰው ደግሞ ሰዎቹ ቋሚ ደንበኞች መሆናቸውና በዚህ መልኩ ሁሉም በተጠየቁት ዋጋ የሚገዙ መሆናቸው ነው፡፡

ቅድም ወዳነሳሁት የዘይት ጉዳይ ልመልሳችሁ። አንዳንዶቹ ሶሞኑን የዘይት ዋጋ መናር በተለይ የምርት ማነስ፤ በሩስያና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት የጥሬ እቃ መወደድ ወዘተ በሚል ያነሳሉ። እንዲህ አይነት ምክንያቶች ግን ጤናማና የሚጠበቁ ናቸው። ውጤታቸው በሂደት የሚያጋጥም እንጂ በድንገት ከላይ ዱብ የሚል አይደለም። እናም ዋናው ምክንያት ሰው ሰራሽ ለመሆኑ ምስክር የሚሻ አይደለም፡፡

የእኛ አገር የንግድ ስርዓት ብዙ ችግሮች ውስጥ የሚያልፍ ነው። አጋጣው ደግሞ ዋነኛ አምራቹም ሆነ ተጠቃሚው የሚጎዱበት ነው። ለምሳሌ የሙዝ ምርትን ስንመለከት አርሶ አደሩ ከስድስት ብር እስከ አስር ብር እየሸጠ ተጠቃሚው የሚገዛው ደግሞ ከ35 እስከ አርባ ብር የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ከቁጥር አንጻር ስንመለከት አብዛኛው አምራች እና ተጠቃሚ ነው። ነገር ግን የዋጋ ንረቱን በማባባስ ሂደቱ ላይ ያሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል መንግስት ህብረተረሰቡ እንዳይጎዳ ከውጭ በሚገቡ የሸቀጥ ምርቶች ላይ ቀረጥ ቢያነሳም ይህ ግን ለውጥ አላመጣም። ይህ ደግሞ መንግስትም የሚገባውን እንዳያገኝ፤ ሸማቹም በአግባቡ ገዝቶ እንዳይጠቀም የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ አካባቢ ያለውን ችግር ከመሰረቱ አይቶ ትክክለኛ መፍትሄ መስጠት ይገባል፡፡

በተለይ መንግስት አንዳንድ ጊዜ ዋጋ ሲንር በመሃል ጣልቃ እየገባ የጥቂት ነጋዴዎችን ሱቅ ብቻ በማሸግ ውጤት አመጣለሁ ብሎ ማሰብ የለበትም። የችግሩን ፈጣሪዎች በአግባቡ አጥንቶ የሚያስተምር ተገቢውን ቅጣት ካልሰጠ አገር የማተራመስ ሃይል ስላለው ሊታሰብበት ይገባል፡፡

ከሁሉ በላይ አንድ የተለመደ ባህል ደግሞ አለ። ዋጋ አንዴ ከናረ በኋላ መልሶ ወደታች መውረዱ የሚታሰብ አይደለም። በዚህ የተነሳ ምክንያት እየፈጠሩ ዋጋ ማናር ከተቻለ ከዚያ በኋላ የሚያወርደው አለመኖሩን የተገነዘቡ ጥቂት ስግብግብ ነጋዴዎች እንዲህ ገበያውን ሲያተራምሱ ዝም ብሎ ማየት እና ለጥቂት ጊዜ ብቻ እቃ በማቅረብ ዋጋን ለማረጋጋት ከመሞከር ይልቅ መፍትሄው ዘላቂ የሚሆንበትን ሁኔታ መፍጠር ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል። ምክንያቱም ይህ ከሽብርተኝነት ተለይቶ የማይታይ አገርን የማተራመስ ተግባር ነው።

# የእኛ ዛሬ በአባቶቻችን ተፈጥሯል፤ የልጆቻችን ነገ በእኛ መልካም ዛሬ ላይ ይፈጠራል

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ኢትዮጵያና ጀግንነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ልክ እንደ እጅና ጓንት፣... ከዘመን ዘመን ከትውልድ ትውልድ ስማችን በኩራት ሲጠራ ቆይቷል። አርበኝነት ከታሪክነት ባለፈ በእያንዳንዳችን ነፍስ ላይ የበቀለ የኢትዮጵያዊነት አለላ መልክ ነው። ብዙ ትላንትናዎችን የፈጠረ የዘመን ቀለማት። ለዚህ ደግሞ በተለያየ ጊዜ በጠላት ላይ በወሰድነው የበላይነት ያስመዘገብናቸው አኩሪ ብሄራዊ ድሎች ምስክር ናቸው። ከነዚህ እሙን የታሪክ ድርሳን ውስጥ አርበኞቻችን ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ።

የትላንቷ ኢትዮጵያ የዛሬዋም መልካም ምድር በአርበኞቻችን እንባና ደም የተቀለመች ናት። ሲነኳቸው በሚቆጡ፣ ሲደፍሯቸው በህብረት በሚነሱ ጥቁር ህዝቦች የጸናች ናት። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በወርቅ ቀለም ከተጻፉ ክቡር ስሞች ውስጥ አርበኛ የሚለው ቃል ቀዳሚው ቃል ነው እላለው። በዘመናት የጥቁሮች ታሪክ ውስጥ ፋና ወጊ ሆኖ ዛሬም ድረስ በክብር ይጠራል። ከአፍሪካ አልፎ በዘመናዊው የአውሮፓ ሥልጣኔ ውስጥ የሃያላኖቹ የእግር እሳት ሆኖ ዛሬም ድረስ አለ። የቆምነው በዚህ ታላቅ እውነት ውስጥ ነው። ኢትዮጵያን ያቆማት ይሄ ስም ነው።

ለአፍሪካም ሆነ ለዓለም ፋና ወጊዎች ሆነን ቀደምት ስልጡን ህዝቦች በመባል የምንጠራው በአገራቸውና በርስታቸው ቀልድ በማያውቁት አባቶቻችን ደምና አጥንት ነው። ከትላንት እስከዛሬ ለአገርና ህዝብ ክብር ሲሉ ራሳቸውን እንደ ሻማ ያቀለጡ በርካታ አባቶች አሉን። ርስቴን አልሰጥም፣ የአገሬን ዳር ድንበር አላስነካም ሲሉ የሞቱ፣ የተንገላቱ ብዙ የአገር ባለውለታ አርበኞች በትላንትና በዛሬ ውስጥ አሉ። እኔና እናንተም የነዚህ ባለውለታ አርበኞቻችን የደም ፍሬ ነን። የዛሬዋ ኢትዮጵያ በዚህ ልክ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልታና ታፍራ እንድትታይ ያደረጉት እነሱ ናቸው። በአድዋና በካራማራ፣ በኡጋዴንና በአንባላጌ ታላቅ ገድልን በመፈጸም የማይሞትና የማያረጅ ዘላለማዊ ክብርን የሰጡን ባላደራ ትውልዶች ነበሩን። ቋያ በታጠቁ ጥቁር ክንዶች፣ ጽናት ባነገቱ ህያው ነፍሶች ከባርነት ወጥተናል። ዘመን በማይሽረው የአርበኝነት ተጋድሎ ብዙ የጠላት ወረራዎችን በድል አልፈናል። በአባቶቻችን ደም፣ በአርበኞቻችን አጥንት በዓለም ላይ ታላቋን የነጻነት ምድር ኢትዮጵያን ፈጥረናል።

እኔም እናንተም የአባቶቻችን የድል ፍሬዎች ነን። ክብራችን ሳይጎድል፣ ነጻነታችን ሳይነካ ዳር ድንበራችን ሳይደፈር ከትላንት እስከዛሬ በክብር የምንጠራው ነፍሳቸውን ለአገር በሰጡ አባቶቻችን ሞት ነው እያልኩ ነው። ሁላችንም የሞት ፍሬ ነን። የዛሬው እኛነታችን በዚህ ልክ የተገኘው ሞት በተከፈለበት የዛኛው ትውልድ ጀብድ ነው። በአባቶቻችን ደም የበቀልን በአጥንታቸው የታፈርን የብዙ ተጋድሎ ውጤቶች ነን። ብዙዎች በሚናፍቁት ማንም በሌለው አገራዊ ታሪክ ውስጥ የምንኖር ሕዝቦች እንዲህም ነን። በታላቅ ክብርና ሞገስ ከትላንት እስከዛሬ ተራምደናል። ለኢትዮጵያ ክብርና ነጻነት ደማቸውን ባፈሰሱ እውነተኛ የሕዝብ ልጆች ከጭቆና ወተን አንገታችንን ቀና አድርገናል። ኢትዮጵያን ተባብረው በገነቧት ጽኑ ክንዶች ታቅፈን ወደ ሚደነቅ ብርሀን ተሸጋግረናል። በአባቶቻችን ብዙ ሞትና መከራ አርነት ወጥተን ስማችንን በታሪክ ድርሳን ላይ ጽፈናል። ክብር ለዛኛው ትውልድ ይሁንና..።

ከእውነት ሁሉ እውነት አገር ናት። አገር የሁላችን ክብር ናት። የደስታችን አጥቢያ የሐዘናችን መድረሻ እንዲህም ናት። ስለ አገር አባቶቻችን ያስተማሩን እውነት ይሄ ነው። ከታላላቆቻችን የሰማነው፣ ከፊተኞቻች ያወቅነው ጥበብ ይህ ነው። በነፍሶቻችን ላይ የአባቶቻችን የአደራ ቃል አለ። ይሄን የአደራ ቃል ይዘን ነው የምንኖረው። አርበኝነት በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ያለ፣ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ደም ውስጥ የሚቀዳ የሉአላዊነት ድንበር ነው። የእያንዳንዳችን ትላንት፣ የእያንዳንዳችን ዛሬና ነገ በአርበኞቻችን ሞት የተገኘ ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንደ ድርና ማግ ፈትለውና ሸምነው በትውልድ ልብ ውስጥ የቋጩ የዚህኛውም የዚያኛውም አለም ጀብደኛ ነፍሶች ናቸው። በእኚህ ነፍሶች ውስጥ መኖር ለአገርና ህዝብ የሚከፈል የዜግነት ግዴታ ይመስለኛል። በነዚህ ነፍስ ውስጥ መኖር ራስን ለሌሎች ህልም ገምሶ እንደመስጠት እቆጥረዋለው። በአባቶቻችን ደጋግ ነፍሶች ዛሬ እኔና እናንተ ወልደን ከብደን እድሜ ቆጥረናል። ብርቱ ሕዝብ፣ ስልጡን አገር ተብለን በዓለም አደባባይ ተመስክሮልናል።

> ተነጋግሮ በመግባባት ለሌሎች የምናስፈልግበት፣ ለሌሎች የምትሆን ምቹ አገር ለመፍጠር የአርበኝነት ሥራ የምንሰራበት ሰዓት ላይ ነን። ዛሬ መልካም ነገር ለመስራት ከቀኖች ሁሉ ትክክለኛው ቀን ነው። በዚህ ቀን ላይ መልካም ስራ በመስራት በእኛ በኩል ለሚመጣው አዲስ ትውልድ ስንቅ ለመሆን መነሳት ይጠበቅብናል። የእኛ ዛሬ በአባቶቻችን የተፈጠረ ነው። የልጆቻችንም ነገ በእኛ መልካም ዛሬ የሚፈጠር ይሆናል። የሀሳባችን መልካም መሆን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ላሉም በረከትና መልካምነትን ነውና ሁሉን ነገር ከሀሳብ እንጀምር። ህልምና ራዕያችን ለሌሎች እንዲጠቅምና እንዲበጅ አድርገን እናዘጋጀው

ነገ ለሚፈጠረው አዲስ ትውልድ ደግሞ እኔና እናንተ እናስፈልጋለን። በአባቶቻችን ሀቅ እንደኖርን ሁሉ በእኛም ሀቅ የሚኖር ትውልድ ይመጣልና ራሳችንን ለኃላፊነት ማዘጋጀት ይኖርብናል። አባቶቻችን በዚህ ልክ ባይኖሩ ኖሮ አሁን ላይ እኛ በዚህ ልክ አንገኝም ነበር። አባቶቻችን ለእኛ እንዳስፈለጉ ሁሉ እኛንም የሚፈልግ ትውልድ ይመጣልና አስፈላጊ ዜጋዎች ሆነን መቆም የዜግነት ግዴታችን ነው። በአባቶቻችን መኖር ኖረናል። በተስፋቸው ለምልመናል፣ በእውነታቸው ደምቀናል አሁን ሌሎችን ለማኖር የእኛ ተራ ነው።

ተነጋግሮ በመግባባት ለሌሎች የምናስፈልግበት፣ ለሌሎች የምትሆን ምቹ አገር ለመፍጠር የአርበኝነት ሥራ የምንሰራበት ሰዓት ላይ ነን። ዛሬ መልካም ነገር ለመስራት ከቀኖች ሁሉ ትክክለኛው ቀን ነው። በዚህ ቀን ላይ መልካም ስራ በመስራት በእኛ በኩል ለሚመጣው አዲስ ትውልድ ስንቅ ለመሆን መነሳት ይጠበቅብናል። የእኛ ዛሬ በአባቶቻችን የተፈጠረ ነው። የልጆቻችንም ነገ በእኛ መልካም ዛሬ የሚፈጠር ይሆናል። የሀሳባችን መልካም መሆን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ላሉም በረከትና መልካምነትን ነውና ሁሉን ነገር ከሀሳብ እንጀምር። ህልምና ራዕያችን ለሌሎች እንዲጠቅምና እንዲበጅ አድርገን እናዘጋጀው።

አባቶቻችን የኢትዮጵያ የትላንት ብሩህ መልኮች ነበሩ። አርበኞቻችን ለእያንዳንዳችን ደማቅ ዛሬ የሞት ዋጋ የከፈሉ የመልካም ልቦች ባለቤት ነበሩ። ሁላችንም ለሁላችን እናስፈልጋለን። ሁላችንም አስፈላጊዎች ሆነን ነው ወደ ምድር የመጣነው። በአባቶቻችን የአርበኝነት ተጋድሎ ዛሬ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ተፈጥረዋል። ነገ ደግሞ በእኔና በእናንተ የአርበኝነት ተጋድሎ የሚፈጠር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ይኖራል። ከእኛ በኋላም ያለው ትውልድ እርስ በእርሱ የሚደጋገፍ ነው። ደምቀው የተጻፉ ብዙ ትላንትናዎች በእያንዳንዳችን ዛሬ ውስጥ አሉ። ለህይወታችን እጅግ አስፈላጊ ሆነው አጠገባችን የቆሙ ሰዎች ነበሩ። ለመኖራችን ብርታት ሆነው በትላንትና በዛሬአችን ውስጥ የበቀሉ ደጋግ ነፍሶች ስለመኖራቸው አልጠራጠርም። ይሄን እውነት ወደ አገርና ህዝብ ስናመጣው አርበኞቻችንን እናገኛቸዋለን። አርበኞቻችን የእኔና የእናተ የጋራ እውነት ናቸው።

በዓለም አደባባይ ብዙዎች አንገታቸውን ቀና ማድረግ ተስኗቸው አቀርቅረው በሚኖሩበት በዚህ ዘመን ቀና ብለን እንድንራመድ፤ ማነህ ስንባል ኢትዮጵያዊ ነን ብለን በኩራት እንድንናገር ያደረጉን እነሱ ናቸው። በጥቁርነት ውስጥ ዘለዓለማዊ ክብርን፣ ዘለዓለማዊ ነጻነትን ያጎናጸፉን በዛኛው ትውልድ ማህጸን ውስጥ የበቀሉ ዓርበኞቻችን ናቸው። ዛሬ በአገራችን ላይ ጀብድ ለመስራት የእኔና የእናንተ ተራ ነው። ዛሬ የእኔና የእናንተ የድል የተስፋ ቀን ነው። ታሪክ ከማውራት ወጥተን ታሪክ የምንሰራበት ዘመናችን ነው። እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በብዙ ችግርና መከራ ውስጥ የምትገኝበት ሰዓት ላይ ናት። ከትላንት በባሰ የእኛን አንድነት የእኛን አብሮነት የምትፈልግበት የችግር ጊዜ ላይ ናት። ከውስጥም ከውጪም ጠላቶች ተነስተውባታል። አንድነቷን ህብረቷን ለመሸርሸር የተንኮል ሴራዎችን የሚያሴሩ ግለሰቦች ቡድኖች አገሮች ሳይቀሩ የተነሱበት ጊዜ ነው። እንደ አባቶቻችን ትውልድ የማይረሳውን የጀግንነት ተግባር ፈጽመን ለማለፍ ትክክለኛው ሰዓት ላይ እንገኛለን።

ከእኔነት ወጥተን ለአገራችን ምርጡን ለማድረግ በአንድነት የምንቆምበት የተጋድሎ ጊዜ ላይ ነን። አባቶቻችን በዓድዋ ጣሊያንን፣ በካራማራ ሶማሊያን፣ እንዲሁም በሌሎችም የጦር ግንባር ዘምተው በአርበኝነት በርካታ ድሎችን በማስመዝገብ ዛሬ ላለችው ኢትዮጵያ ምሳሌ ሆነዋል። እኛም ነገ ለምትፈጠረው አዲሷ አገርና አዲሱ ትውልድ የሚሆን አኩሪ ስራን የምንሰራበት ጊዜ ላይ ነን። እንደ አባቶቻችን የኢትዮጵያዊያን ደማቅ ቀለሞች ሆነን ስማችንን ከትውልድ አብራክ ውስጥ እንጽፍ ዘንድ ዛሬ የእኛ ቀን ነው። አገራችን በውስጥም በውጪም እዬዬ እያለች ነው። ብዙ እንባዎች፣ ብዙ ዋይታዎች የሚሰሙበት ሰሞን ላይ ነን። የሕዝቦች በአንድነት መቆም ግድ የሚልበት የጭንቅ ሰዓት ላይ ነን። በፖለቲካው በኢኮኖሚው በማህበራዊው ህይወታችን ውስጥ አገራችን የእኛን አርበኝነት የምትፈልግበት ጊዜ ላይ ነን። አሁን ለአገራችንም ሆነ ለሕዝባችን ምርጡን የምንሰራበት ከሁሉ ምርጥ ወቅት ላይ እንገኛለን። ኢትዮጵያን እወዳለው የሚል ሁሉ ከወሬነት ባለፈ በተግባር የሚፈተንበት ጊዜ ነው።

እኔ የአገሬ ለቅሶ ይሰማኛል። እንድንረዳት በእናታዊ አሳዛኝ አይኖቿ ስታየኝ ያታለው። የአገሬ በአንድነት ተነሱ ድምጽ ይሰማኛል። የኢትዮጵያ ህመም የእያንዳንዳችን ህመም ነው። በመከራዋ ውስጥ መከራችን አለ። ዛሬውኑ እንዳባቶቻችን በአንድነት በመቆም የአገራችንን ችግር እልባት መስጠት ይኖርብናል። አብዛኞቹ ችግሮቻችን አንድነትን ህዝባዊነትን የሚሹ ናቸው። አብዛኞቹ መፍትሄዎች ደግሞ በእኔና በእናንተ እጅ ውስጥ ናቸው። እኔና እናንተ በአንድነት ከቆምን ችግሮቻችን ሁሉ እሳት እንዳየው ቅቤ ቀልጠው እንደሚጠፉ ጥርጥር የለኝም። የእስካሁኑ ችግሮቻችን በአንድነት ማጣት በመለያየት የመጡ ናቸው። ባለመነጋገር፣ ባለመደማመጥ የተፈጠሩ ናቸው። መለያየታችን የፈጠራቸው ችግሮቻችን ናቸው ዛሬ ላይ በየቦታው መከራ ሆነው የሚያሰቃዩን። አርበኛ ለመባል የግድ ጦር ሜዳ ሄደን መዋጋት አይጠበቅብንም። አርበኛ ለመባል ጦርና ጎራዴ ወይም ደግሞ መሳሪያ መታጠቅ አይኖርብንም። በብዕራችን መልካም ነገር በመጻፍ አርበኛ መሆን እንችላለን። በተግባራችን አስፈላጊዎች በመሆን ታሪክ መስራት እንችላለን። በእያንዳንዱ አገራዊ ችግር ላይ በነቃ ተሳትፎ መፍትሄ በማምጣት የዚህኛው ትውልድ አርበኛ መሆን እንችላለን።

እንደ አገር ለሚነሱብን አፍሪካዊም ሆነ አለም አቀፍ ተቃውሞዎች በአንድነት በመቆም ጀብድ መስራት እንችላለን። በተሰማራንበት የስራ መስክ ላይ አገርና ሕዝብ የሚጠቅም አመርቂ ውጤት በማምጣት አርበኛ መሆን እንችላለን። ጥሩ ነገር በመስራት፣ መልካም ነገር በማሰብ በዙሪያችን ላሉ አስፈላጊዎች ሆነን በመቆም በዚህም አርበኛ መሆን ይቻላል። መልካም ሥራ ለመስራት ከተዘጋጀን ጀብድ ልንሰራባቸው የምንችልባቸው በርካታ አገራዊ ጉዳዮች አሉ። ችግሩ ግን ካበደው ጋር ማበድ፣ ድንጋይ ካነሳው ጋር ድንጋይ ማንሳታችን ነው።

አገራችን በአስተሳሰባችን ውስጥ ናት። ከቆሻሻ አስተሳሰብ ወጥተን ወደ ሚደነቅ ብርሀናዊ እውነት መምጣት ይኖርብናል። አብዛኞቻችን ታሪክ ከመስራት ይልቅ ታሪክ በማውራት የምንኖር ነን። ዛሬ ላይ ታላቅ ነገር ለመስራት ከመሞከር ይልቅ በአክሱምና ላሊበላ እየተደነቅን ስራ ፈተን የምንቀመጥ ብዙዎች ነን። ትልቅ ለመሆን ከመጣር ይልቅ ትልቅ ነበርን ብለን ያለፈን በማውራት ጊዜ የምናጠፋም ነን። ትልቅ ነገር ለመፍጠር ከተዘጋጀን ይቻለናል። አባቶቻችን ባልዘመነና ባልሰለጠነ ዘመን ነው አለምን ጉድ ያስባለ ታሪክ የሰሩት። እኛም የዛሬዎቹ ትውልድ በብዙ ነገሩ ምቹና ስልጡን በሆነ ዘመን ላይ ነን፤ ለህዝባችንም ሆነ ለአገራችን ታሪክ ለመስራት ከመቼውም ጊዜ በላይ ምቹ ዘመን ላይ ነን። የአባቶቻችንን ወኔ ለብሰን ላሉብን አገራዊ ችግሮች መፍትሄ በማምጣት፤ የሚያግባቡንና ችግሮቻችንን የሚያራግፉልን ከፍ ያሉ ሃሳቦችን በማመንጨት የዜግነታችንን እንድንወጣ በማሳሰብ ላብቃ። **ሰላም!**

# «የመሬት አጠቃቀም እቅድን በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል»

- ዶክተር ጌታቸው ድሪባ
በግብርና ዘርፍ አማካሪ

ዘላለም ግዛው

የኢትዮጵያን እርሻ በዘላቂነትና በመዋቅራዊ መልክ መለወጥ አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል። ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ፣ የኢትዮጵያን ግብርና እመርታ ውስጥ የሚያስገቡ የፖሊሲና የቴክኖሎጂ ለውጥ አምጪ ሃሳቦች በኢትዮጵያ ተግባራዊ መደረግ ጀምረዋል። ከእነዚህ መካከል የበጋ ስንዴ የመስኖ ልማት ይጠቀሳል። በዚህ ውስጥ የእርሻ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በስፋት ማዳረስም ትኩረት ይሻል። ከሕገ መንግሥቱ ጋርም በማይጋጭ መልኩ የመሬት የንብረት ባለቤትነትን ጥያቄ የመፍታት፣ የገጠር ብድር አገልግሎትንም ማስፋፋት ለዘርፉ ለውጥ ወሳኝ ከሆኑት መካከል መጥቀስ ይቻላል።

የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና እና የምግብ ሥርዓቱ ዙሪያ በዓለም አቀፍ የተባበሩት መንግሥታት ያገለገሉትና አሁን የኢትዮጵያ ግብርና ዘርፍን በማማከር በማገልገል ላይ የሚገኙት ከዶክተር ጌታቸው ድሪባ ጋር በነበረን ቆይታ በተጠቀሱትና በተያያዥ ጉዳዮች ትኩረት አድርገን የተነጋገርነውን እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

**የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ወቅታዊ ሁኔታ**

የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና እና የምግብ ሥርዓት የቆየ፤ የስልጣኔ ምንጭ እንደነበረ መገንዘብ ያስፈልጋል። በዘመኑ አዝርዕቶች ተገኝተዋል። ከብቶች ተላምደዋል። የእርሻ መሳሪያዎች ተፈጥረዋል። የእርሻ ሥርዓቱ እስከዛሬ ድረስ ይዞ ያለው በዛን ዘመን የተፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ብቻ ነው።

ለተከታታይ ዘመናት ዕድገቶች እንዲታዩ፤ ውጤቶች እንዲኖሩ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ምርጥ ዘሮችን፣ ማዳበሪያን፣ የትራክተር እርሻን የማስተዋወቁ ሥራ በሰፊው በዘመቻ ደረጃ የተካሄደበት ጊዜ ነበረ። በተለያዩ መንግሥታትም ከፍተኛ ዕድገት እንዲመጣ ጥረት ተደርጓል። ነገር ግን የተደረገው ጥረትና የደረስንባቸው ውጤቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደረሰበት የሕዝብ ዕድገት የምግብ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም አልሆነም።

እንደሚታወቀው ስንዴ፣ ሩዝና የምግብ ዘርያዎች ከወተት ተዋጽኦ ጀምሮ በአብዛኛው በከፍተኛ ዋጋ ወደ አገር እያስገባን ነው። ይህ ደግሞ ባለፉት 20፣ 30 እና 40 ዓመታት እያደገ መጥቶ ከፍተኛውን የአገርን የውጭ ምንዛሪ እየወሰደ ይገኛል። በጥቅሉ መመዘኛ የሚሆነው ዕድገት አለ ሳይሆን፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ እንዳላሳካ መመልከት ይቻላል።

ለዚህም ሁለት ነጥቦችን መመልከት አስፈላጊ ሲሆን ቀዳሚው አስቸኳይ የምግብ ርዳታ የሚፈልጉ ሕዝቦች ቁጥር መጨመር ነው። በተለይ በከብት ማርባት የሚተዳደሩ አርብቶ አደሮች ከፍተኛ የምግብ ዋስትና መቃወስን በአንድ በኩል መመልከት እንችላለን። በሶማሌ ክልል፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በቦረና አካባቢ በድርቅ ምክንያት የተከሰተውን መመልከት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ምግብ ነክ ነገሮችን ከውጭ ማስገባቷ ከሚወጣው የውጭ ምንዛሪ ባሻገር የዓለም ፖለቲካ አሰላለፍ የዩክሬንና የራሺያ ጦርነት የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና በከፍተኛ ደረጃ እይታ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ጦርነቱ የራቀ ቢሆንም የዓለም ሕዝብ ኒዩክሌር ቦንብ እንዳይፈጠር ቢያሳስበውም ለኢትዮጵያ ግን በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮች ርቀን የምግብ ዋስትናው እንደኒዩክሌር ቦንብ ሆኖ እያሰጋ ነው።

ዩክሬንና ራሺያ በድምሩ በዓለም ንግድ ገበያ ያቀርቡት የነበረው የ25 በመቶ የዓለም ንግድ ድርሻ ሲገታ በዓለም ላይ የምግብ ዋጋ ንረቱ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል። መንግሥት በድጎማ ቢይዘውም በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ መናርም ከማጓጓዣ ሰንሰለቱ ጋር ስለሚያያዝ ከፍተኛ ችግር እንደሚያመጣ መመልከት ይቻላል። የማዳበሪያ ዋጋም ከእጥፍ በላይ እየናረ ይገኛል።

የዩክሬንና የራሺያ ግጭት ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም

> የብድር አገልግሎቱ ገበሬዎች የሚሳተፉበት ሁኔታን በምስጢር መልኩ ከተዘረጋ በኋላ ቴክኖሎጂዎች በስፋት እንዲዳረሱና እንዲቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል



ብለን አቻችለን እንኖር የነበረውን በማዛባት ዛሬ በከፍተኛ ደረጃ የመኖር ህልውና ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጓል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና በተገለጹት ነጥቦች ያጠነጥናል።

**የተፈጠረውን ወቅታዊ ችግር እንዴት ማለፍ ይቻላል?**

አሁን የተፈጠሩ ችግሮች መፈታት አለባቸው። የኑሮ ግሽበቱ እና የዋጋ ንረቱ እያንዳንዱ ተመጋቢ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጫና ያሳድራል። ስለዚህ ፈጣን የአጭር ጊዜ መፍትሔ ያስፈልጋል። መንግሥት በዘመቻ መልክ አሁን እያደረገ ያለው የበጋ ስንዴ የመስኖ ልማትን ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ ማምረቱ ጥሩ ነው።

ትግበራውን ከዘመቻ ሥራ ወደ ወትሮና ዘለቄታዊ ትግበራ ማዞር ያስፈልጋል። ተግባሩንም የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያን አካባቢዎች እንዲያካትት አድርጎ መቀጠል ያስፈልጋል። በአጭር ጊዜ ሲታሰብ አሁን የተያዘው የመስኖ እርሻ በተለይም በበጋ ማምረቱን የማስፋት፣ ኅብረተሰቡ ጋር የማድረስ፣ ከፍተኛ እገዛ ማድረግ ግድ ይላል።

በርካታ ዜጎች በምግብ እና በማኅበራዊ ደህንነት ርዳታ ውስጥ ናቸው። አሁን የዳቦ ጥያቄ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደሚደርስ እያደገም እንደሚመጣ መታሰብ ይኖርበታል። በመሆኑም የማኅበራዊ ድጎማ ማድረግ ግድ ይላል። በተለይ የገቢ ደረጃቸው በአነስተኛና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ላሉት በዳቦ ላይ የሚደረገው የዋጋ ጫና ሁሉን አቀፍ ማድረግ ባይቻልም በኑሮ ደረጃቸው ተመዝነው እገዛ የሚደረግበት መንገድ መታሰብ አለበት። መደበቅ የማንችልበት ዘመን መሆኑን የኢትዮጵያ መሪዎች፣ ገበሬው፣ ባለሃብቱ፣ ነጋዴው በጥሞና ማየት አለባቸው።

**ችግሩን ስዘለቄታው ስመፍታት ምን መሠራት አስበት?**

መንገድ የሚያሻግሩና የዘለቄታ ትልም የሚያመጡ የዘላቂ የልማት ግቦች ወይንም 2030 አጀንዳ ተብለው ኢትዮጵያም የገባችበት ቃል ኪዳን ላይ በርካታ ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህ ዙሪያ ኢትዮጵያም የምግብ ሥርዓት ብላ ከተባበሩት መንግሥታትና ከሌሎችም አጋሮቿ ጋር በመተባበር ካለፈው ዓመት ጀምሮ ተግባር ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት ችግር ሊፈቱ ይችላሉ የተባሉ 22 የመፍትሔ ሃሳቦች ይዘው ቀርበዋል። እነዚህ የመፍትሔ ሃሳቦች ሰፋ ያሉ ቢሆኑም በዚህ ዓምድ ስር ስድስቱን መመልከት እንችላለን።

እነዚህ ጉዳዮች የኢትዮጵያን እርሻ በዘላቂነትና በመዋቅራዊ መልክ ሊለውጡ የሚችሉ፣ አሁንም ሆነ ለወደፊቱ ኢትዮጵያን እመርታ ውስጥ ሊያስገቡ የሚችሉ ተብለው የሚታሰቡ የፖሊሲና የቴክኖሎጂ ለውጥ የሚያመጡ ሃሳቦች ናቸው። ሥራውም በግብርና እና በጤና ሚኒስቴር እየተመራ ይገኛል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

### የመሬት የንብረት ባለቤትነት ጥያቄ እንዴት ይፈታ?

የመጀመሪያው ብዙ ወጪም የማያስወጣ ከሕገ መንግስቱ ጋርም በማይጋጭ መልኩ የመሬት የንብረት ባለቤትነትን ጥያቄ የመፍታት ጉዳይ ነው። ገጠሩንና ከተማውን ወጥ የሆነ የፖሊሲ ምንጭ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። ሕገ መንግሥቱም ይህንን ይፈቅዳል።

የመሬትን ሥርዓት የሚያስተዳድር እርስ በእርስ የሚናበብ ሁሉን ኢትዮጵያዊ እኩል የሚያደርግ፣ ተዘዋውሮ የመኖር፣ ሃብት የማፍራት ጉዳይ ላይ መሥራት ያስፈልጋል።

የመሬት ጉዳይ ከ1967 ዓ.ም መሠረታዊ ለውጥ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ ማሻሻያዎች ቢደረጉበትም የሕዝብ ዕድገቱና የግብርና ዘርፉ ፍላጎት ጋር ሊሄድ አልቻለም። በገጠር የሚገኘው ሕዝብ እየተዋለደና እየኖረ በከተማ ደረጃ የተወሰነ ፍልሰት ቢኖርም አሁንም በዛው እርሻ ላይ ይገኛል።

ይህ የመሬት መበጣጠስን በማስከተል የአንድ ሄክታር አንድ አስረኛ በሆነ መሬት ላይ ኑሮውን የሚመራው የቤተሰብ ብዛት አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ነው። 12 ሚሊዮን የሚሆኑ ገበሬዎች ደግሞ የሚተዳደሩት ከግማሽ ሄክታርና ከዛም በታች በሆነ መሬት ነው። በዚህ ላይ ብዙ ለውጥ ማምጣትም ብዙ ማምረትም አይቻልም። በነፍስ ወከፍ ምርታማነትን ማምጣት አይቻልም።

የምርት ዕድገት መጥቷል ተብሎ ቢገለጽም የምርት እድገት የመሬቱ የምርታማነት መጨመር፣ በተወሰኑ አርሶ አደሮች ከጎረቤት አገራት ሊወዳደር የሚችል የመሬት ምርታማነት ሊኖር እንደሚችል ያሳያል። ነገር ግን እያንዳንዱ ገበሬ ምርታማነቱ አናሳ ነው።

በአንድ አስረኛ ሄክታር ላይ የሚመረት ምርት ሊያሳድግ፣ የኢኮኖሚ ውጤትን፣ የማኅበራዊ ደኅንነትን፣ የምግብ ዋስትና ምን ያህል ሊያመጣ ይችላል? የሚለውን መመለስ ያስፈልጋል። ስለዚህ የመሬት ጥያቄን ሕገ መንግሥቱ የሕዝብ ብሎ አስቀምጦታል። በዛው ድንጋጌ ውስጥ ደግሞ የመሬት ባለቤትነትን በአንቀጽ 40 ገበሬው የሊዝ መብት ተሰጥቶት መሬቱን አስይዞ መበደር፣ በገጠር የእርሻ ዘርፍ የመሬት ጉዳይ በሕጋዊ መንገድ ማስተላለፍ የሚችልበትን መንገድ በጥናት በመመሥረት ኪሳራ በማያስከትል ሁኔታ መፈታት ይችላል። ይህም ለመሪዎች ቀርቦ ውሳኔ ሊያሰጥ በሚችል ደረጃ ላይ ነው።

በተበጣጠሰ መሬት ቴክኖሎጂን እና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ከባድ እንደሆነ መንግሥትም ገብቶታል። የኩታ ገጠም እርሻ ለማስፋፋትም ያዳግታል። አንድና ሁለት ዓመት ምርታማነት ያድጋል። በዛ ጊዜ የሚገኘው ዕድገት የተወሰኑ ሰዎችን ሊጠቅም ይችላል። ነገር ግን አርሶ አደሩ ሃብት ማፍራትና መሸጋገር ካልቻለ ጊዜያዊ ዕድገት ቢገኝ የዘለቄታ እድገት አይሆንም።

### የገጠር ፋይናንስና የብድር አገልግሎት

ሌላው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ እስከዛሬ ድረስ ከፍተኛ ማነቆ ሆኖ ያለው በርካታ የኢትዮጵያ የፖሊሲ አውጭዎች በቅርበት ያላዩት በሩቅ ብቻ የሚመለከቱት የብድር ወይም የእርሻና የገጠር የፋይናንስ አገልግሎቶችን በቅርበት፣ በስፋት አነስተኛ አርሶ አደሮችን ሊያግዝ፣ ካፒታላቸውን ሊያሳድግ የሚችልና የእነርሱን ሕይወትና ህልውና ያማከለ የፋይናንስና የብድር አገልግሎት አለመኖር ነው።

ባለፉት 20 ዓመታት የፋይናንስ ሴክተሩ በተለይም የግልና የመንግሥት ባንኮች በስፋት መጥተዋል። ይህ በጎ ነው። የንግድ ባንኮች የግሉም ሆነ የመንግሥት የሚያበድሩበት፣ የሚመሩበት የብድር ሥርዓታቸው ከግብርናው ዘርፍ ጋር የሚጣጣም፣ የሚደጋገፍና የሚገናኝ አይደለም። ግብርና አደጋን ያማከለ፣ በተፈጥሮው በእሳት፣ በጎርፍ፣ የዝናብ ወቅትን ጠብቆ ባለመዝነብ፣ በድርቅ፣ በአዝዕርት ተባዮች በሽታዎችና በተለያዩ ችግሮች እያለፈ የሚሄድ ዘርፍ ነው።

የመንግሥትና የግል የፋይናንስ ዘርፉ እያበደረ ያለው በሚታወቅ አንድ አካባቢ ላይ ተበትኖ ባለው ወይንም በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ ነው። ይህንን ዘርፍ በቀላሉ መምራት ይቻላል። የግብርና ዘርፉ ግን ሰፊ ነው። ግለሰቦች በትናንሽ ቦታዎች ላይ በተለያዩ የስጋት ቀጠናዎች የሚኖሩ ናቸው። በመሆኑም የግብርናው ዘርፍ የተለየ የፋይናንስና የብድር አገልግሎቶች ሊፈቀድለት ይገባል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በአማራ፣ በትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ በደቡብ የፋይናንስ ዘርፎች ተብለው በቅርብ ጊዜ ተፈጥረዋል። እነርሱ እያደጉ ናቸው። በተቻላቸው መጠን ለግብርናው ዘርፍ የተቻላቸውን ያህል በማበርከት አስተዋጽኦ እያደረጉ ያሉ ድርጅቶች ናቸው። ጥሩ ነው። ግን የኢትዮጵያ የግብርናው ዘርፍ ከሚፈልገው ጋር የሚጣጣም ዕድገት አይደለም።

> **የመሬት አጠቃቀም እቅድን በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል**

የግል የንግድ ባንኮች ከግብርናው ጋር የሚያገናኛቸው በጣም ውስን ነው። እነርሱ ደግሞ የመሬት ጥያቄው በዋስትና መሬትን ማስያዝ አይቻልም። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለአንድ ገበሬ ብድር መስጠት የሚችለው 30 ሄክታርና ከእዛ በላይ ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ 30 እና ከእዛ በላይ ሄክታር መሬት የአነስተኛ ገበሬ ዘርፍ አንድም የለም። ስለዚህ ብድር እሰጣለሁ የሚለው በሌለው ዓለም ውስጥ ነው።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ብድር እሰጣለሁ የሚለው ከፍተኛ ሄክታር 20 ሺህ እና ከዛ በላይ ላላቸው ነው። የኢትዮጵያ ገበሬ የሚኖረው በግማሽ ሄክታር፣ አንድ ሄክታር ውስጥ ነው። የብድር አገልግሎት ለማግኘት የሚችልበት አይደለም። ይህም ከፍተኛ የሆነ ማነቆ፣ ከድህነት ወደ ድህነት፣ ከችግር ወደ ችግር እየሄደ ያለ የኅብረተሰብ ክፍል የሚዳረስ የፋይናንስ አገልግት አለመኖሩን ያሳያል።

የሌሎች አገራትን ተሞክሮ ብንወስድ የእርሻ አብዮት ከገጠሩና የእርሻ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን የዓለም የእርሻ ታሪክ ያሳያል። ኢትዮጵያም ወደ እዛ መግባት አለባት። በቅርብ ዘመን ቻይና በ15 ዓመታት ውስጥ የግብርናውን ዘርፍ በገንዘብ በመደገፍ የእርሻ አብዮት ካካሄዱ አገራት አንዷ ናት። የተለያዩ የግብርና ዘርፍ ባንኮች የተለያዩ የብድር አገልግሎቶች በከፍተኛ ደረጃ ያሳደገች አገር ናት።

ከምዕራባውያን በተለይም ከእንግሊዝ፣ ከመካከለኛው አውሮፓ ከ17ኛው እና 18ኛው ከኢንደስትሪ አብዮቱ ጋር ተያይዞ እርሻን ለማሳደግ የተጠቀሙበት የብድርና የገጠር ልማት ፋይናንሲንግ እንደምሳሌ መጠቀም እንችላለን። እንደሁኔታውም በኢትዮጵያም እያንዳንዱ አይነት የብድር አገልግሎት የሚገኝበት ራሱን የቻለ ተቋም ይዞ መሄድ ያስፈልጋል።

### የእርሻ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በስፋት ማዳረስና ፈጠራ

እርሻ በኢትዮጵያ ያረጀ ያፈጀ ግን የስልጣኔ ምንጭ ነው። ዓለም ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የገባበት መድረስ ቀርቶ ኋላ ቀር ነው። በመሆኑም አሁን የሚጠበቀው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በስፋት ማዳረስ ያስፈልጋል። የብድር አገልግሎቱ ገበሬዎች የሚሳተፉበት ሁኔታን በምስጢር መልኩ ከተዘረጋ በኋላ ቴክኖሎጂዎች በስፋት እንዲዳረሱና እንዲቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል። የተወሰኑትን ብንጠቅስ ትራክተር፣ መሰብሰቢያ ማሽን፣ ኮምባይነር በስፋት ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል። እነዚህን ለማስተዋወቅ በ1960ዎቹ በስዊድኖች የአርሲ የገጠር ልማት ድርጅት፣ የወላይታ ሶዶ፣ የቆቦ አላማጣ የሚባሉ የእርሻ ተቋማት ነበሩ። በተለያዩ ምክንያቶች ፕሮጀክቶቹ አልቀጠሉም። ግን የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የነበሩ አካባቢዎች እንደ ባሌ፣ አርሲ፣ ከፊል ሸዋ እነዚህን የእርሻ መሳሪያዎች በስፋት ተጠቃሚዎች ናቸው።

የባሌና የአርሲ የስንዴና የገብስ ቤት ተብለው የሚጠሩት እነዚህን ተገን አድርገው በመሥራታቸው ነው። አብዛኛው ተረፈ ምርት ከጤፍ ውጭ የሚመጣው ከእነዚህ ሁለት አካባቢዎች ነው። ኢትዮጵያ በታሰበና በታቀደ አንዱ ሌላውን እየደገፈ በሚሄድበት ሁኔታ እነዚህን ቴክኖሎጂዎችን ማምጣት ያስፈልጋል። በአንድ ወቅት የእርሻ መሣሪያዎችን የመገጣጠም ሥራ ተጀምሮ ነበር። ነገር ግን በሙስና ችግር ምክንያት ሥራው ለመሬቱ የማይሆን የብረት አይነት ባለመቅረቡ ምክንያት ተስተጓጉሏል። ለኢትዮጵያ የአፈር አይነት የመሬት ይዞታ ታሳቢ ያደረገ የእርሻ ትራክተሮች፣ ኮምባይነር፣ ኸርቨስተሮች፣ መከስከሻዎችን በጥልቀት ተመልክቶ ከሌሎች ጋር አጋርነት ፈጥሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገጣጠምበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

የማዳበሪያ ጉዳይም ወሳኝ ነው። የዩክሬን ጦርነት የነበረንን ችግር አባብሶታል። የማዳበሪያ ዋጋ ከእጥፍ በላይ ጨምሯል። አሁን ተጽዕኖው ባይታይም ጊዜው ደርሶ ማዳበሪያ ተገዝቶ ለአርሶ አደሩ በሚከፋፈልበት ጊዜ ድሮም ዋጋው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የመንግሥት ፖሊሲ አውጭዎች በዚህ ጉዳይ ሊያስቡበት ይገባል።

በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች በመኖራቸው ኢትዮጵያ ማዳበሪያ ማምረት ትችላለች። አፋር ላይ ከፍተኛ የፖታሽ ሃብት አለ። ይህን መሠረት በማድረግ የተወሰኑ የማዳበሪያ ፋብሪካዎችን የማቋቋም ሃሳብ በተቀናጀ መልኩ ሊተገበር ይገባል።

የተሻሻሉ ዝርያዎችን የማምጣት፣ ከብቶችን የማዳቀል ሥራ በከፍተኛ ደረጃ የሚታሰብበትና የኢትዮጵያ የእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት የሚሠራቸውን እንደየአካባቢዎቹ ሊመረጡ በሚችሉበት ዙሪያ አገልግሎት መስጠት አለበት። ትግበራውንም በቅንጅት በመሥራት ለሕዝብ ማዳረስ የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። ትግበራው በቴክኖሎጂና ፈጠራ የኢትዮጵያን ግብርና ማዘመን አካል ነው።

ያለፉት 10 እና 15 ዓመታት ግምገማ ሲታይ ለስንዴና የእህል ውጤቶች በአማካኝ የሚወጣው አንድ ቢሊዮን ዶላር ነው። የገቢ ምርትን ሊያስቀር የሚችል ምርታማነትን መፍጠር ሲቻል ይህንን ካፒታል ኢንቨስትመንት ውስጥ ማዋል ይቻላል። የውጭ ርዳታ ውስጥ ሳንገባ ባለው ሃብት ወደ ዘለቄታ መፍትሄ መምጣት ይቻላል።

### የመሬትና የተፈጥሮ ሃብት መመናመን

ከመሬት መበጣጠስ፣ የተፈጥሮ ሃብት መመናመን ጋር አሁን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንኳን በመኪና በትራክተር ገብቶ ለማረስ ድንበር የሌለበት ሁሉም ሰው መሬቱን እያንዳንዱን ኢንች በከፍተኛ ደረጃ እየተከታተለ ነው። በአንድ በኩል ጦርነትና ግጭት ያስከተለ ሁኔታ ይታይበታል። ስለዚህ የገጠር እርሻ ውስጥ መንገዶችን ማውጣት፣ የትኛው ቦታ ለከብት ርባታ፣ ለከተማ መስፋፋት እንደሚውል ለይቶ ማጥናት ይገባል። ከተማ እየተስፋፋ በጣም ምርታማ የሆኑ መሬቶችን ቀይሯል። ይህ ለዘለቄታው አያዋጣም፣ በትውልድም ነቀፌታን ስለሚያስከትል የመሬት አጠቃቀም እቅድን በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

መሬት ደግሞ እርሻ እየተስፋፋ በመሄዱ ያሉ የተፈጥሮ ደኖች፣ የተፈጥሮ ምንጮችና የተፈጥሮ ሃብቶች እየደረቁ ናቸው። በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ መሪነት በአረንጓዴ አሻራ በዓመት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዛፎች መተከላቸው እሰየው ቢያስብልም የመሬት አጠቃቀም ጉዳይ እርሻ በየትኛው ቦታ መኖር እንደሌለበት የሚደነግግ ሕግ ባለመኖሩ የተበላሸ አሠራር ወንዞች፣ ኩሬዎችና ሐይቆች ሳይቀሩ እየደረቁ ይገኛሉ። የዚህ የመሬት አጠቃቀም በከፍተኛ ደረጃ የሚታሰብበት መሆን አለበት።

### የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለገጠሩ ማኅበረሰብ

ኅብረተሰቡ ማገዶ አንድዶ ለማክሰል፣ ለመብራት ጥቅም ላይ የሚያውለው የተፈጥሮ ሀብትን አመናምኖ እንጨት ቆርጦ ነው። የኤሌክትሪክ አገልግሎት በስፋት እየደረሰ አይደለም። በርካቶች የከተማ ነዋሪ በበቂ ደረጃ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ስለማያገኙና የመቆራረጥ ችግር በመኖሩ በእንጨትና በከሰል የመጠቀም ሁኔታ አለ።

አሁን የህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ዙር ምርት ላይ ነው። በተከታታይ ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ምርት እንደሚቀጥል እየተጠበቀ ነው። ይህ ከፍትሐዊ ተጠቃሚነት ባሻገር ተፈጥሮንም ማዳን ነው። እንጨት ላይ ተመስርቶ ያለውን ኅብረተሰብ ኤሌክትሪክ እንዲጠቀም በማድረግ ተፈጥሮ ሀብትን እንዲጠብቅ የተመናመነውን መልሶ እንዲገነባ፣ ከአረንጓዴ አሻራ ሥራ ጋር የማቀናጀት ሥራን ይጠይቃል።

ከሕዳሴ ግድቡ የሚገኘው ኤሌክትሪክ ኃይል ለጎረቤት አገራት በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ታሳቢ ተደርጎ የተሠራ ነው ቢባልም፤ ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ለኢትዮጵያ ገበሬና ለገጠር ሕዝብ እንዲዳረስ ማድረግ ነው። ከእነርሱ ከተረፈ የውጭ ምንዛሪ ለማስገባት መታሰብ ያለበት። የፀሐይ ኃይልን ጥቅም ላይ ማዋልም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

### ኢንሹራንስ

እርሻ በተፈጥሮው ስጋት ያለበትና ለአደጋ የተጋለጠ የሥራ ዘርፍ ነው። የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት ካለበት ደረጃ ለማሻገር ተገቢ ሥራ ቢተገበርም ተፈጥሮ አንዳንዴ ትቀጣናለች። በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በጎርፍ፣ በግጭትም የብዙ ጊዜ ኢንቨስትመንትም በአንድ ጊዜ ሊወድም ይችላል። በመሆኑም አርሶ አደሩ ኢንሹራንስ ገብቶ በሙሉ ልቡ በኢንቨስትመንቱ እንዲሳተፍ ቢደረግ መልካም ነው።

መንግሥት ከመደበኛ በጀት ላይ ወስዶ ኅብረተሰቡን እየቀለበ ነው። ለወደፊቱ ግን ይሄ በዘለቄታነት መቀጠል አይችልም። ገበሬው ራሱን ኢንሹራንስ ገብቶ በተለይ የሕክምና አገልግሎት እያገኘ ነው። በተጨማሪም ለሚደረሰው አደጋ ኢንሹራንስ ገዝቶ እንዲጠቀም ማድረግ ይገባል።

### ማጠቃለያ

የኢትዮጵያን እርሻ ስራ ከነበረበት፣ አድጓል የሚባለው እውነታነት ቢኖረውም ከኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት ጋር አይናበብም፤ አቅርቦትና ፍላጎቱም አልተጣጣመም። አሁን ከቀውሱ እየተወጣ ነው። ግብርናውን ለማዘመን አዲሱ የኢትዮጵያ አመራር ፊቱን ወደ ኢኮኖሚው ማዞር፣ ኃይሉን የመጠቀምና የሚያስፈልጉ ከላይ የተመለከቱ ዐቢይ ጥያቄዎችን የሚመልስ አሰራርን መፍጠር ይጠበቅበታል። ኢትዮጵያውያንም የንግዱን፣ የኢንዱስትሪውን ዘርፎች እርሻን የሚደግፍ በማድረግ እየተደጋገፈ የሚሄድ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ፋይዳ

**አስመረት ብስራት**

ኢትዮጵያ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብ ከምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ስትሆን ከአፍሪካ አምስተኛ ደረጃ ላይ መቀመጧን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። በዚህም የቻይና ኩባንያዎችም በአገሪቱ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ቀዳሚ ተዋናዮች በመሆን 43 ቢሊዮን ብር ፈሰስ እያደረጉ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከቻይናና ከሌሎች አገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚፈሰው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መጨመሩን ተከትሎ ኢትዮጵያ ለውጭ ኢንቨስተሮች ምቹ መዳረሻ እየሆነች መምጣቷን ፤ በኢትዮጵያና ቻይና ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብርና ትስስር መፈጠሩን፤ ይህን ተከትሎ በርካታ የቻይና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ መሰማራታቸው የሁለቱ ሀገራት ትስስር እየጎለበተ መሆኑን አመላካች ነው።

በኢትዮጵያ ፈሰስ የተደረገውን የቻይናውያንን ኢንቨስትመንት ከሌሎች ሀገራት ጋር ስናነጻጽረው የላቀ ነው። በዚህም ኩባንያዎቹ በአገሪቱ ዕድገት ላይ የማይተካ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ያመለክታል። በተጨማሪም በርካታ ኩባንያዎች ከእስያ፣ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከቻይና፣ ከአውሮፓና አውስትራሊያ ወደ አገሪቱ እየገቡ መሆኑን ያመላክታል። ነገር ግን በርካታዎቹ ኢንቨስተሮች ከቻይና የሚመጡ ሲሆኑ የዚህ ምክንያት ደግሞ ኢትዮጵያ ያላት እምቅ የኢንቨስትመንት አቅም መሆኑንም መረጃው ያመለክታል።

የተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ኮንፈረንስ በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት መሠረት ኢትዮጵያ ባላት አዎንታዊ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታ በምሥራቅ አፍሪካ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመሳብ ቀዳሚዋ አገር መሆኗን ጠቅሷል። ከአፍሪካ ደግሞ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅ፣ ኮንጎና ሞሮኮን በመከተል አምስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች።

በርካታ የውጭ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ የመረጡበት ምክንያት አገሪቱ ምቹ የሆኑ የኢኮኖሚ መዳረሻዎች ያሏት ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በዓለም በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኝ ኢኮኖሚ ባለቤት ከመሆኗ ባለፈ ምቹ የሆነ የገበያ ዕድል ያለባት አገር በመሆኗ ነው። ከዚህ ባለፈ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በጣም አስፈላጊ የሆነውን መሠረተ ልማት አሟልታ መያዟንም ተመራጭ ከሚያደርጓት ጉዳዮች መካከል ነው።

በኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በቻይናውያን ኩባንያዎች ተይዘው ወደ ሥራ የገቡና በዝግጅት ላይ የሚገኙ አንድ ሺ 564 ፕሮጀክቶች ይገኛሉ። እነዚህ ፕሮጀክቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ውስጥ ዋነኛ ተዋናዮች ሲሆኑ በፕሮጀክት ቁጥርና በፋይናንስ አቅርቦት ቀዳሚ መሆናቸውንም መረጃው ያመላክታል።

ከላይ ባስቀመጥነው መረጃ መሰረት ኢትዮጵያ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስተሮችን መሳቧ ምን ይጠቅማታል? ለህዝቡስ ምን ጠብ የሚል ነገር ያመጣል? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ይሄንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይዘን የቀድሞ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የነበሩትን አቶ ብርሃነ መዋን አነጋግረናል። እሳቸውም ሀገር በተስተካከለ የኢኮኖሚ መደላደል ላይ እንድትቀመጥ የማምረት አቅም ከአገልግሎቱ ዘርፍ መብለጥ ይኖርበታል። ስለዚህም አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሀገሪቱ መግባታቸው ክፋት የለውም ይላሉ።

መጀመሪያ ከመግዛት በፊት መስራት መፍጠር ለገበያ የሚቀርብ ነገር መኖር ይኖርበታል የሚሉት አቶ ብርሀነ፤ እንዳለመታደለ ሆኖ ሀገሪቱ በርካታ ፋብሪካዎች ከሚኖሯት ይልቅ በርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሞልተው ይገኛሉ። እነሱም ለአገልግሎታቸው የሚሆነውን ምርት በሀገር ውስጥ ገበያ ስለማያገኙ የውጭ ገበያን ማማተር ይኖርባቸዋል። ለዚህም ደግሞ የውጭ ምንዛሪን ማግኘት የግድ የሚል ይሆናል። የውጭ ምንዛሪ የማግኘት ጉዳይ ደግሞ በአብዛኛው በእርሻ ላይ የተንጠለጠለ መሆኑ ካለው ውስን የውጭ ምንዛሪ ላይ አብዛኛውን የአገልግሎት ዘርፉ ከወሰደው ለእድገት ፤ ለቴክኖሎጂ በጣም አስፈላጊ ለሚባሉ ነገሮች የሚወጣ ገንዘብ አይኖርም። ስለዚህም ግብርናውንም ቢሆን እሴት ጨምሮ የተሻለ ምንዛሪ የሚያስገኝ የሀገር ውስጥን ፍላጎት በሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች በተመረቱ ነገሮች ለመሸፈን ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መኖራቸው ግድ የሚል መሆኑን ይናገራሉ።


ፎቶ- አዩብ ተፈሪ

አቶ ብርሀነ መዋ

> “የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅጣጫ የውጬ ባለሀብትን ማስገባት ከሆነ እሱ ጥሩ ነው። ሀገሪቱን በዘላቂነት ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችልና በውጬ ላይ ያለን ጥገኝነት በመቀነስ በራስ መተማመን እንዲኖር ለማድረግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ለዚህም የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገባ የማበረታታት ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።”

የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ሲገቡ ትልቁ ነገር ካፒታል ይዘው መግባታቸው ነው። ፋብሪካቸውን አቋቁመው ስራ ሲጀምሩ በርካታ ሰዎችን መቅጠር፤ በግብር የሀገር ኢኮኖሚን መደገፍ ብሎም ምርታቸውን ወደ ውጭ ሀገር ሲልኩ ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ማምጣት በኢንቨስትመንቱ እናገኛቸዋለን ብለን ከምናስባቸው ጥቅሞች መካከል መሆናቸውን አቶ ብርሃነ ያብራራሉ።

ይህም ትክክለኛ የሆነ ፖሊሲ ማስቀመጥ ከተቻለ የሀገር ጥቅምን ባስቀደመ መልኩ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር እንዲገቡ ከተደረገ ይዘውት የሚመጡት ቴክኖሎጂ ሀገር ልታሳካው የምትፈልገውን የኢኮኖሚ መደላድል ከመፍጠር አንፃር ጠቀሜታ አለው። ኢንቨስተሮቹ ስራቸውን ጨርሰው ለቀው የሚሄዱ ከሆነም ኢትዮጵያውያን በስራው ውስጥ ገብተው መስራት የሚችሉበት አቅም ቢፈጠርላቸው ውጤቱ የላቀ እንደሚሆን አቶ ብርሃነ ያስረዳሉ። ይህም እንዲሆን የውጭ ኢንቨስተሮች በአቋቋሟቸው ኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ዜጎች በቀጣይ ሊያሰራቸው የሚችል በቂ እውቀት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ስርአትም ሊኖር ይገባል።

የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገሪቱ ሲገቡ በቴክኖሎጂ፤ በእውቀት ሽግግር ሀገሪቱ በቀጣይ ልትጠቀምበት የምትችለውን ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸት ሀገሪቱ ለምታልመው ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ መደላድል ይፈጥራል። የውጭ ባለሃብቶች በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ሁኔታ ካልተመቻቸ የሰሩትን ስራ ትርፍ ወደ ሀገራቸው ይዘውት መሄዳቸው የማይቀር መሆኑን በመረዳት ወደ ሀገር በመግባታቸው የሚገኘው ተጠቃሚነት እየቀነሰ እንዳይሄድ አግባብነት ባለው ፖሊሲ ዘርፉ መመራት ይኖርበታል ሲሉ አክለዋል።

ይህም ሲባል የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገሪቱ ሲገቡ በርካታ ስራ አጦችን የሚቀጥር ኩባንያ ሊሆን ይገባዋል። ከዚህ በላይ ግን የሰራተኛ ቅጥሩ በደንብ የተጠናበት የሰራተኛውን መብት መጠበቅ ያለበት መሆኑን ይናገራሉ። የውጭ ምንዛሪን ለማምጣት ኤክስፖርት ገበያ ከታሰበ ሊመጣ ይችላል። በትኩረት መታየት ያለበት ጉዳይ ግን የውጭ ምንዛሪ ማምጣቱ ላይ ብቻ ሳይሆን የውጭ ምንዛሪ ያስወጣል ወይ የሚል ጥያቄ መጠየቅ አለበት። ምን ያህል ጥሬ እቃ ነው ከውጭ የሚያስገባው? የሀገር ውስጥ ምርትን እንደግብአት ይጠቀማል ወይ? ምርት ወደ ውጭ መሄዱ ብቻ ሳይሆን ለሀገር ውስጥ የሚተርፍስ ይሆናል ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ መሆን ይኖርበታል። ይህ ሲባል የሀገር ውስጥ ህዝብ እየተራበ ወደ ውጭ ለውጭ ምንዛሪ ሲባል ከመላክ ለሀገር ውስጥም የሚተረፍ ነገር ሊኖር ይገባል። የሀገርን ጥቅም ያስቀደመ የቀጥታ ኢንቨስትመንት ፖሊስ ሊኖር እንደሚገባ አቶ ብርሃነ ያብራራሉ።

ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ እንደ ትልቅ ቁም ነገር መታየት ያለበት ኢትዮጵያ በማንኛውም አይነት የፍላጎት ምርቶች ራሷን መቻሏ ነው፤ ትልቁ ሀገርን በዘላቂነት የሚጠቅመው ይሄ ነው። በጊዜያዊነት የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት፣ ሰራተኛ ለመቅጠር ሊሆን ቢችልም ትልቁ ቁም ነገር የኢትዮጵያን ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ ማረጋገጠ፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ተጠናክሮ ኢኮኖሚውን መያዝ ሲችል ያኔ ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ መፍጠር የሚቻል በመሆኑ ዘርፉ ትኩረት ይሻል ይላሉ።

በውጭ ኢንቨስተሮች ላይ የሚንጠለጥል ኢኮኖሚ በቀላሉ የሚፍረከረክ ይሆናል። የአለም አቀፍ ኢኮኖሚ እና የውጭ ኢንቨስትመንት ላይ መንጠልጠል እነሱ ባኮረፉ ቁጥር አንታዘዝም ባልን ቁጥር፣ እርዳታ እና ብድር እናቆማለን ከሚሉ ማስፈራሪያዎቻቸው ባሻገር ኢንቨስትመንታችንን እናወጣለን በማለት ይወጣሉ። በተለያዩ ጊዜያቶች የውጭ ኢንቨስትመት በፖለቲካ የሚጠለፍበት ሁኔታ መኖሩንም የሰሞኑ የሩስያና የዩኩሬን ጦርነት ታላቅ ምስክር መሆኑን ይናገራሉ። በአጠቃላይ የውጭ ኢንቨስተሮች መምጣታቸው ችግር ባይኖረውም በዘላቂነት ግን የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ቀዳሚ ሆኖ ሌሎቹ ተከታዮች መሆን ይገባል።

የውጭ ባለሃብት መሳብ ጥሩ ቢሆን የሚመጡበት ምክንያት ግን ግልፅ ሆኖ መቀመጥ አለበት። የሚመጡበት አለማ ግልፅ ይሁን ሲባል፤ ባለሀብቱ በመምጣቱ ሀገሪቱ የምታተርፈው ምንድነው የሚለው መታየት አለበት። የውጭም ሆኑ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች መዋእለ ነዋያቸውን አፍስሰው ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጠብ የሚል ነገር የሚያበርክቱ ከሆነ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል።

አሁን ላይ የሚታየው በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ባለሀብቶች በይበልጥ ለውጬቹ የበለጠ ድጋፍ መደረጉ ከላይ እንዳልነው ኢኮኖሚው የውጭ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲጠለጠል ያደርገዋል ማለት ነው። ስለዚህም ይዘው ለሚመጡት ነገር ተመጠጣኝ የሆነ ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር የሀገርን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች የተለየ ድጋፍ ሊደረግላቸው የማይገባ መሆኑን አቶ ብርሃነ ያስረዳሉ።

“ሀገሪቱ ውስጥ የኢንቨስትመንት ዘርፉ ምን ይጎለዋል? ምን ቢደረግለት ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ይደርሳል? በሚል የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ ጥናት ያስፈልጋል” የሚሉት አቶ ብርሃነ፤ ጥናት ላይ ተሞርክዞ ትክክለኛ ጉድለቱ ከታወቀ በኋላ ፖሊሲው ጥናትን መነሻ አድርጎ የሚወጣ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ። ጉድለቶች እየታዩ ለኢንዱስትሪዎቹ የተለያዩ ድጋፎች ሲደረጉ ሀገሪቱን የማይጎዳ ሌሎችንም በተለየ የማይጠቅም መሆን የሚኖርበት ሲሆን የግድ አስፈላጊ የሆኑ የሚባሉ ነገሮችን ግን በጥናት አይቶ መደረግ ያለበትን ማድረግ ይገባል የሚል ምክረሀሳብ አላቸው።

በአጠቃላይ ዘርፉ የታሰበውን ያህል ከፍ እንዳይል አሁን ሀገሪቱ ያለችበት የጸጥታ ችግር ነው የሚሉት አቶ ብርሃነ ፤ ይህ ማለት ሰው ገንዘቡን አፍስሶ ስራ ለመስራት የተመቻቸና ሰላም የሚሰጥ የስራ አካባቢ እንዲኖር መንግስት ኃላፊነት ሊወስድ የሚገባ መሆኑን አሳስበዋል።

“የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅጣጫ የውጭ ባለሀብትን ማስገባት ከሆነ እሱ ጥሩ ነው ፤ ሀገሪቱን በዘላቂነት ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችልና በውጭ ላይ ያለን ጥገኝነት በመቀነስ በራስ መተማመን እንዲኖር ለማድረግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ለዚህም የሀገር ውስጥ ባለሃብቱ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገባ የማበረታታት ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።” ብለዋል።

በቅርቡ በሀገሪቱ በስንዴ እርሻ ላይ የተጀመረው ስራ አበረታች መሆኑን የተናገሩት አቶ ብርሃነ፤ የሀገሪቱን የስንዴ ፍላጎት በሀገር መሸፈን ከተቻለ መሰረታዊ ፍላጎቶቻችንን ከውጭ የማንፈልግ ከሆነ ለቴክኖሎጂና አዲስ ነገር ለማግኘት የውጭ ኢንቨስተሮች መጋበዝ ጉዳት አይኖረውም።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ማበረታታት ችግር ሲመጣ ወደ ውጭ ከማየት የሚያድን መሆኑን ጠቁመው፤ በቅርቡ ዘይት ችግር ሆኖ መነሳቱ በጣም ያሳዝናል። ከ20 አመታት በፊት በየአካባቢው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ያቀርቡ የነበሩትን ማስወገዱ ስህተት መሆኑን ጠቅሰው፤ የሀገር ውስጥን አቅም ሊያሳድግ ይገባል ብለዋል።

ባጠቃላይ መንግስት በተለይ መሰረታዊ በሆኑ ፍጆታዎች ምርት ላይ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን ቢያበረታታ በተጨማሪነት ግን ለተሻሉ ቴክኖሎጂዎች የሚያመጣ፤ ለበርካታ ስራ አጦች የስራ እድል የሚሰጥ የውጭ ምንዛሪ የሚያመጣ ጠቀሜታቸው ከሚያስወጡን በላይ ከሆነ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ሀገሪቱ መግባታቸው የሚበረታታ ነው በማለት ቆይታችንን ቋጭተናል።

# ጎሜ

# ፈጅቶ ከሚያጠግበኝ እስኪበርድ ይራበኝ

**ሙሉቀን ታደገ**

የዩናይትድ ኪንግደም ጠቅላይ ሚኒስትር እና ተዋቂ ጸሃፊ የነበረው ቤንጃሚን ዲዝራኤሊ እንደተናገረው አለም የምትገዛው ተራ ሰው እንደሚያስበው የስልጣን ወንበር በተቆናጠጡት ሰዎች አይደለም። አለም የምትገዛ ባለስልጣናትን በሚቆጣጠሩት እና የአገዛዝ ፍልስፍና ወይም ርዕዮተ አለሙን በሚቀርጹ ከትዕይንቱ በስተጀርባ ባሉ ሰዎች ነው ።ይህን አባባል ስመለከት አይተ ጭሬ ልድፋው መሰረትኩት ያለውን መንግስት ያስታውሰኛል።

በህዝብ ላይ በፈጸመው ግፍ ከስልጣኑ የተባራረው የአይተ ጭሬ ልድፋው ከመጋረጃ ጀርባ በሚያሽከረክሩት የጥፋት ሹፌሮቹ ተገፋፍቶ ከሃገራችን ህግና አሰራር ውጭ መንግስት መሰረትኩ አለ። መሰረትኩት ያለው መንግስትም በእነሚስተር ቶማስ እርዳታ ካልተደረገለት እና በእነ ደባልቄ አሸብር እንዲሁም በእነሱሌማን አወል ፈቃድ እርዳታ ማመላለሻ ኮሊደር ካልተፈቀደለት እንደ መንግስት ይቅርና እንደ ህዝብ መኖር አይችልም ። ያለጨው በርበሬ ያለሞፈር በሬ ማለት ይህ አይደል?

የአይተ ጭሬ ልድፋው መንግስት የኢኮኖሚ አማራጮችን ከመመልከት ይልቅ እርዳታን በመጠባባቅ መንግስት ነኝ የሚል የአለማችን ብቸኛው መንግስት ነው። ጂኒየስ ቡክ ኦፍ ሪኮርድስ እስከ ዛሬ እንዴት እንዳልመዘገበው ይገርመኛል ።በነገራችን ላይ የአይተ ጭሬ ልድፋው መንግስት በእርዳታ ላይ የተንጠለጠለ የአለማችን ብቸኛው መንግስት ሆኖ ሳለ ጂኒየስ ቡክ ኦፍ ሪኮርድስ አለመመዝገቡ ጂኒየስ ቡክን በራሱ በጂኒስ ቡክ ላይ ሊያስያመዘገበው ይገባዋል ባይ ነኝ ።በአስቸኳይ ጂኒየስ ቡክ ኦፍ ሪኮርድስ የማይመዘግበው ከሆነ የውጭ እርዳታ አሰባስብንም ቢሆን ጂኒየስ ቡክ ኦፍ ርኮርደስን ጨምሮ የሚመዘግብ ሌላ ተቋም በአገራችን ማቋቋማችን የማይቀር ነው።

በጠራራ ጻሃይ ህንጻ በመሸጥ የምትታወቀው ዮዲት እንዲህ ሆኖ መንግስት መሆን ከተቻለ እኔንም ከስራዬ አባሩኝ እና ለእኔም እርዳታ እንዲሰጠኝ ተመቻችቶልኝ ዘመድ አዝማዶቼን አሰባስቤ መንግስት ልመሰርት ማለቷን ሰማን። ለአምባገነኖች እና የግብዞች መልካም ተሞክሮ ማለት ይህ አይደል!

በአዲስ አበባ እና በሌሎች የሃገሪቱ ክፍሎች የጠፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እና የተሰወሩ ዩኒቨርሲቲ ህንጻዎች የት እንደገቡ ሳይታወቁ የውሃ ሽታ የሆኑት ብቻቸውን ሳይሆን አይተ ጭሬ ልድፋው እና ግብረ አበሮቹን ለአመታት በቂ ሁኔታ ከሚያስተዳደር ገንዘብ ፣ ሃሽሽ፣ ውስኪ እና ከመሳሰሉት ነገሮች ጋር ይመስለኛል።ቢሆን ነው እንጂ የአይተ ጭሬ ልድፍው እና ግብረ አበሮቻቸው ረሃብ ተከሰተበት ተብሎ ሰዎች በግፍ ከሚሰደዱበት አካባቢ እነሱ ውስኪ ከቁርጥ እያማረጡ መኮምኮማቸው።

የሆነው ሆኖ ውስኪን በህንጻ፤ ተራራን ከእህል ጋር ቀላቅለው የሰረቁት ግብዞች ለራሳቸው «ወዲ እከሌ ወዲ እከሌ» እያሉ ቅጽል ስም እየሰጡ በሰረቁት ንብረት ማፈር ሲገባቸው የሰፈራቸውን ሰዎች እኛ ሰፈር ውስጥ መኖር ካልቻልክ አደጋ ተጋርጦብሃል ሲሉ ሰበኩ ። ለጦርነትም መለመሉ ። መከራ የተፈረደበት ህዝብም እውነት መስሎት ወዲ እከሌ በህይወት የማይኖር ከሆነ የእኛ ሰፈር ህዝብ እንደህዝብ መኖር አይችልም ሲል ለራሱ ነገረ ።

ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል፤ በቅሎ ጥሎ ይረግጣል እንዲሉ አይተ ጭሬ ልድፋው እና ግብረ አበሮቹ ለበርካታ አመታት ከስንት እና ስንት ክፍቶቻቸው እና ሃጢያታቸው ጋር ተሸክሞ በፈለጉት የአለም ሀገራት አንቀባሮ ያኖረን ህዝብ ሊያመሰግኑት ሲገባቸው ከመሃል አገር ከጠፋው ኮንዶሚኒየም እና የዩኒቨርሲቲ ህንጻ ጋር የሰረቁትን ውስኪ ከሃሺሽ ጋር ቀላቅለው እየማጉ ጥጋባቸው አላስችል ብሎአቸው የራስ አሉላን ልጅ ከአውሬ የሚጠብቃትን እና የሚንከባከባትን ባለቤቷን ጥላ እንደምትረግጠው በቅሎ ሆኑበት ።ክፉኛም ጎዱት።

ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ እንዲሉ፤ ለራስ አሉላ ልጅ ይበጃል የተባለው አይተ ጭሬ ልድፋው የሰፈሩን ሰው በረሃብ አለንጋ እያስገረፈው ይገኛል ። ጦርነቱን አቁማችሁ ህዝቡን በርሃብ አለንጋ ከመገረፍ የማታድኑት ለምንድን ነው? ተብሎ የተጠየቀው አይተ ጭሬ ልዳፊው «ህዝቡን በርሃብ አለንጋ አታስገርፉት የምትሉ ከእኛ ውጭ ህዝቡ መቼ ጠግቦ ያውቃል? የሚኖረው በሴፍትኔት አይድል እንዴ? ሲሉ ይሞግታሉ። ታዲያ በሴፍትኔት የሚኖርን ህዝብ ራሱን በምግብ እንዲችል በማድረግ ፋንታ ስለምን ለጦርነት ታሰልፉታላችሁ? ተብለው ሲጠየቁ ዋይ ! ህዝቡን ለጦርነት አሰልፈን አገርን ካላበጣበጥን እንደፈለግን የምንሆንበት ገንዘብ ማን ይሰጠናል? ሲል ጥያቄን በጥያቄ መመለስ ይቀናቸዋል። ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ የሚባለው እንደዚህ አይነት አጋጣሚ አይደል ።

አይተ ጭሬ ልድፋው በእርዳታ ላይ የተመሰረተ መንግስት መመስረቱ ብቻ አይደለም የሚገርመው፤ እርዳታ ሊገባባቸው የሚችሉ ቀዳዳዎችን ሁሉ በራሱ መድፍ እና ታንክ ጥርቅም አድርጎ መዝጋቱ ነው ። እርዳታ የሚገባባቸውን መንገዶች በራሱ መድፍ እና ታንክ ጠርቅሞ እየዘጋ ስልምን እርዳታ የሚያመላለሱ ካሚዮሎች (ተሽከርካሪዎች) እንዳይገቡ ይከላከላል ብሎ እሪታውን ያቀልጠዋል ።

ገድሎ በአለቃዬ፤ ከሰሰ በጠበቃዬ እንዲሉ፤ አይተ ጭሬ ልዳፊው ራሱ በራሱ ችግር ፈጥሮ አገርን ካወከ በኋላ ምግብ እና እርዳታ አልደርሰኝ ብሎ ከመጋረጃ ጀርባ እንደፈለጉ ለሚያዝዙት ምዕራባዊያን ድረሱልኝ ይላል። የሚገርመው ምንም ምን የአልሚ ምግብ አይነቶችን ለሰፈሩ መቅረብ እንዳለበት እንኳን የሚመርጠው አይተ ጭሬ ልድፋው እንጂ ረጂ ድርጅቶች አለመሆናቸው ነው ።ይህን ተከትሎ የአለም የዕርዳታ ድርጅቶች ምን አይነት አልሚ ምግብ በብዛት ይቅረብላችሁ ብለው በጠየቁ ጊዜ አይተ ጭሬ ልዳፋው ምን ቢል ጥሩ ነው ዋይ! ለእኛ የምንፈልገው አልሚ ምግብ በአንደኛ ደረጃ ሀሺሽ ፣ ውስኪ እና ጫት ነው ።በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የጦር መሳሪያ ነው። የእኛ ሰፈር ሰው እንደሆነ እርሃቡን ለትግል በርሃ ከገባን ጊዜ ጀምሮ አላምደነዋል ።ስለዚህ ምንም ምግብ አያስፈለገውም ። ማሽላ እና በቆሎ ከሆነ በሚቀጥለው የመኸር ወቅት ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ከአመረቱት ከአጎራባች ክልሎች በምናውቀው ዘዴ እንሰርቃለን! ሃሳብ አይግባችሁ ብሎ አረፈው ።

አይተ ጭሬ ከበፊትም ጀምሮ አለምን የሚያስገርም ንግግር በማድረግ ይታወቃል ።ለምሳሌ «ደብል ዲጂት» የኢኮኖሚ እድገት ፣ በአፍሪካ በእድገት ጎዳና ላይ ያለች ብቸኛ አገር ወዘተ የሚል ጉራ መታወቂያው ነው ።አሁንም ይህ አመሉ አለቅ ብሎት በአንድ በኩል በአስቸኳይ እርዳታ ያስፈልገኛል ።እርዳታው ባስቸኳይ ካልደረሰ እኔ እና የሰፈር ሰዎች ልናልቅ እያለ ለአገኘው ሁሉ ይጮሃል። በሌላ በኩል ራሽያ በዩክሬን ላይ እያደረገች ያለውን ጦርነት ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግስት አለማውገዙ ስላበሳጨኝ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ልጀምር እችላለሁ ሲል ተደመጠ ።እማማ ሁሉ አገርሽ ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት ያሉት እንደዚህ አይነቱን አይደል።

እርዳታን ተማምኖ መንግስት እመሰርታለሁ ብሎ ማሰብ በሀገር ላይ የሚያስከትለውን የከፋ ጉዳት ተመልክተናል። ሃገራችንን ለማበጣበጥ የሚፈልጉ ሃይሎችም ይሄን እንዴት ሲጠቀሙበት እንደነበር ተመልክተናል። የውጪውስ መቼም የውጭ ነው ፤ እኔን የገረመኝ በአገራችን ተወልደው ያደጉ በአገሪቱ አሉ የሚባል ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች በአገሪቱ ሰላም እንዳይኖር ሲጥሩ ስመለከት ነው ።

በቀደም ዕለት የማማ ሁሉን ላንች ልጅ አቶ መርዳሳ ኢብሳ የተባለው ባለስልጣን ከአይተ ጭሬ ልድፋው ካስነሳው ጦርነት ጋር ተያይዞ በአገራችን የተፈጠረውን ያለመረጋጋት ቀዳዳ ተጠቅሞ አገር ለማስበጥበጥ በማሰብ ያለፈው ወር የጊዎርጊስ ዕለት ከአራት ኪሎ ቤተ መንግስት እስከ ምኒሊክ አደባባይ ባለው አስፋልት ድንጋይ በመደርደር ከፍተኛ ጩኸት እና ግጭት በመፍጠር የአገሪቱን ሰለማ ለማወክ ሲሯሯጥ ነበር። ይህን ተከትሎ የፌደራል ፖሊስ ጽጥታውን ለማስጠብቅ አስቦ ሁከት በተፈጠበት አካባቢ ተገኘ ። ፖሊስም ለምን የአገሪቱን ሰላም ትበጠብጣላችሁ? ብሎ መንገዱን በድንጋይ የዘጉ ሰዎችን ማወያየት ጀመረ። ወዲያውኑ ለምን መንገድ እንደዘጉ ለመናገር በርካታ ሰዎች እጃቸውን እንደ ጭራሮ አንጨርፍፈው አወጡ። አቤት ፍጥነት ! ፖሊስም በየተራ እንዲናገሩ እድል ሰጠ።



አይን ነሽ፤ ጥርስ ነሽ ሳይል ሁከት ፈጣሪዎችን በቆመጥ ሲዠልጥ የሚታወቀው ፌዴራል ፖሊስ ያለወትሮው ሁከት የፈጠሩትን አካላት እያወያየ እንዳለ ያዩት እማማ አረጋሽ ሰዎችን ሰብስቦ እያነገረ ያለው የፌዴራል እንባ ጠባቂ ወይስ የፌዴራል ፖሊስ ሲሉ ባለቤታቸውን አቶ ደሰለኝን ጠየቁ ።አቶ ደሳለኝም የጊዎርጊስ፤ የጊወርጊስ የፌዴራል ፖሊስ ላለመደባደብ መሃላ መግባቱን አልሰማሽም ሲሉ ለባለቤታቸው መለሱ።

መንገድ ከዘጉት አንዱ ለምን መንገድ እንደዘጋ ለፖሊስ ምክንያቱን ሲናገር ምን ቢል ጥሩ ነው ! እውነት ለመናገር በአጼ ኃይለ ስላሴ ላይ የተፈጸመው መፈንቀለ መንግስት በታሪክ ሳነብ እጅግ በጣም ይገርመኛል ። የአሁኑ ትውልድ ደግሞ መፈንቀለ መንግስት እንዴት እንደሚካሄድ ተሞክሮ የለውም። ስለሆነም መፈንቅለ መንግስት እንዴት ማድረግ እንደሚቻል በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት ስለሚያስፈልገው በአጼ ሃይለስላሴ ላይ የተፈጸመው መፈንቀለ መንግስት ሲካሄድ ትእይንቱ እንደገና ይደገምልን ብሎ አረፈው ።ፖሊስም የአመጸኛውን ሰውዬ ወደ ኦነግ ሸኔ እንዲቀላቀል ምክር ቢጤ ሊሰጠው አስቦ ኦነግ ሸኔን ከተቀላቀለ በቀጣይ ህግን ለማስከበር በሚኖረው ግዳጅ ላይ ስራ ያበዛብኛል ብሎ አሰበ ። ወደ ቂሊንጦ እንዳይወስደውም ታራሚዎችን እንደሚበጠብጥበት አሰበ ።በዚህ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ የተጋባው ፖሊስ የውጭ ወታደር ልቀጥር እፈልጋለሁ ላለችው ዩክሬን መልምሎ ወደ ዩክሬን እንደላከው ሰማን።

ፖሊስ የአጼ ኃይለ ስላሴ መፈንቀለ መንግስት ትዕይንት ይደገምልን ባለው ልጅ ግብዝነት ተገርሞ ሳይጨርስ ሌላ ጎፈሬውን ያበጠረ ልጅ ከመቀመጫው ተነስቶ እኔ ለዚህ አመጽ የገፋፋኝ ጉዳይ የፓርላማው ሰዓት ስንት አመት ሙሉ ሳይንቀሳቀስ ስለተመለከትኩ በዚያ ተሰምቶኝ ነው አለ ።ፖሊሱም ቀበል አድርጎ ምን ለማለት ፈልገህ ነው ? ሲል ጎፈሬውን ልጅ ጠየቀው። ጎፈሬውም ልጅ አምና ምርጫ ስናደርግ የፓርላማው ሰዓት እንደሚንቀሳቀስ ተስፋ አድርጌ ነበር። ነገር ግን ይሄው ዘንድሮም ሰዓቱ እንደዚህ ቀደሙ ሁሉ ባለበት እንደተቀመጠ ነው። ምንም ሲንቀሳቀስ አይታም። ስንት መንገድ እና አጥር በመዲናችን ብሎም በአገራችን ሲታደስ ለምን ሰዓቱ አይታደስም? ሲል ፖሊሱም ቅኔው ወዲያወኑ ገብቶት እውነትህን ነው የፓርላማው ሰዓት እንዲንቀሳቀስ ቢደረግ ኖሮማ የፌዴራል ፖሊስም ይህን ያህል ስራ አይበዛበትም ነበር ሲል ለጠያቂው ምላሽ ሰጠ። የሚገርመው በአንድ ሰልፍ በመርህ እና በአላማ ደረጃ ፍጹም አራምባ እና ቆቦ የሆኑ አመጸኞች የተሳተፉበት እና አብዛኛው አመጸኛ ደግሞ ምን እና ለምን እንዳመጸ አለማወቁ ነው።

ፈረስ ቢጠፋው ኮርቻውን ገልጦ አየ እንዲሉ እኛ ኢትዮጵያዊያን ችግራችን ምን እንደሆነ እያወቅን ለችግራችን ሁነኛ መፍትሄ ከመለግ ይልቅ በሰፈር በቡድን በቡድን እየተከፋፈለን መነታረክ ይቀናናል ።የእኛ ችግር በልቶ ማደር ነው። የእኛ ችግር ለብሶ ማደር ነው ።የእኛ ችግር ድህነት ነው። እንዲሉ መጀመሪያ ይሄንን ችግር እንደፖለቲከኛ ድህነትን ተጋፍጠን አንገብጋቢ የሆነውን እና መቅደም ያለበትን ችግር መፍታት ሲያቅተን የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ፣ መብት ወዘተ እያልን ስልጣናቸውን ማራዘም ይቀናናል ።ድንቄም ፖለቲካኛ ! ሰውን አባልታችሁ አስጨርሳችሁ ማንን ልትመሩ ነው ?

«ፈጅቶ ከሚያጠግበኝ እስኪበርድ ይራበኝ» እንዲሉ አሁን ላይ ለእኛ ኢትዮጵያዊያን የቸገረን የብሔር ብሔረሰቦች መብት ፣ እኩልነት ወዘተ እየተባለ ፖለቲከኞች ለጥቅማቸው የሚፈተፍቱት ነገር አይደለም። እኛ የቸገረን አይተ ጭሬ ልድፋው እና መሰሎቹ ለአመታት ሲከዝኑብን የኖሩት ድህነት ነው ።ስለዚህ ሁሉም ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ስለእውነት ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስብ ከሆነ ድህነትን የምናሸንፍበትን መንገድ ያሳየን።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## መፍረስን መጥሳት በ"አንፈርስም አንታደስም" ውስጥ

ተገኝ ብሩ

ግጥም ስሜትን ልዩ በሆነ መልክ ያመላክታል፤ የውስጥ ሀሳብን በተለየ መልክ ይገልፃል። ማህበረሰብን ለማነፅ ሰበብ ይሆናል ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይን ለማሄስ ብሎም ለማረቅ ግጥም ያለው ቦታ ከፍተኛ ነው። እንዲህ ቢሆን አልያም እንደዚህ መሆን አልነበረበትም ወይም ደግሞ እየሆነ ነው በተራ ቋንቋ ከመግጠም ባለፈ ጉዳዩ በግጥም ተዋዝቶ ሲነገር ድምፀቱ ይጎላል። ሀሳብን ልዩ በሆነ መልኩ አስውቦ በተመረጡና ቁጥብ ቃላት በተመጠነ ቀለም ተሳክቶና ዜማ እንዲላበስ ተሰናስሎ ይቀርባል።

ሀሳብን በጎላ መልኩ ከሚገልፁ የግጥም መፅሀፍት ውስጥ አንዱ መርጠን ከመሀሉ ደግሞ የሀሳብ ግዝፈቱ የጎላውን ልናስመለክታችሁ ስለወደድን ነው፤ ግጥምን መግለጥ የተያያዝነው። የዛሬ ቅኝታችን በአሌክስ አብረሀም አንፈርስም አንታደስም የግጥም መድብል ውስጥ ያገኘነው አንድ ግጥም በሀሳብ ትልቀቱ ከፍ ያለ ሆኖ አግኝተን መርጠነዋል።

በተባ ብዕሩ በአዲስ የአተራረክና ታሪክ ነገራ ስልት ብቅ ብሎ ብዕርህ አይንጠፍ ያልነው ወጣቱ ደራሲ አሌክስ አብረሀ በ2009 በታተመው "አንፈርስም አንታደስም" በተሰኘ የግጥም መድብሉ ውስጥ ያካተተውን "እግዜርን እሰሩት" የተሰኘ ግጥሙን በዚህ ፅሁፌ ውስጥ በራሴ አተያይ ለመግለፅ ሞክሬያለሁ።

አሌክስ በዚህ ግጥሙ:- ማህበረሰባዊ ልማድ፣ ፖለቲካዊ ሽሙጥ በአጠቃላይ የማህበረሰባችን እና የመንግስት አስተዳደር ባህሪና አጠቃላይ ገፅታ አጉልቶ በሚያሳዩ ልዩ አገላለፅ፣የቃላት አጠቃቀም ማህበራዊ ሂስና ትችት ጥልቅ በሆነ እይታ ይዘረዝራል።

አሌክስ በ "እግዜርን እሰሩት" በተሰኘው ግጥሙ በተመጠኑ ቃላት ገላጭ በሆኑ ውብ ስደራ ኢትዮጵያዊ በሆኑ ዘይቤዎች ይጠበባል።እኔም የአሌክስ አብረሀምን ምልከታ የዚህ ወቅት አጠቃላይ ማህበራዊ ገፅታችን በትክክል ያሳያልና እንማርበትም በስነፅሁፉም እንዝናናበት ብዬ በዚህ መልክ እሱ ያሳየኝን ወደማሳየት ገባሁ።

አሌክስ አብረሀም "እግዜርን እሰሩት" በተሰኘ ግጥሙ ማህበረሰባዊ የበዙ ጉዳዮች በተለይም ለየት ያለ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በራሱ መነፅር አጉልቶ ለማሳየት ይሞክሯል። በግጥሙ የተገለፁት በተለይም ፖለቲካዊ ባህሪያትን በሚዘረዝር ምልከታው የአምባገነንነት ጥጉ ምንነት የእብሪተኝነት ልኬት መገለጫው የተበላሸ ስርዓትና አስተዳደር ባህሪው አቅም ያላቸው ቃላት በመጠቀም ይገልፃል።

ግጥሙ እጅግ በጣም ረጅምና እያንዳንዱ የግጥሙ ርዕሰ ጉዳይ ክፍሎች የተለያዩ ትልልቅ ጉዳዮችን አጉልቶ የሚያሳይ በመሆኑ ግጥሙን አንድ ላይ ከመተንተን ይልቅ ሀሳቡ በግጥሙ መሀል እየገባው ለመግለፅ እሞክራለሁ። አንባቢው ይህንን ፅሁፌን ሲያነብ ግጥሙ አንድ ወጥ መሆኑን እንዲገነዘብና እኔ ሀሳቡን በገባኝ ልክ ለማብራራት ብዬ መሀሉ እየገባሁ እንደቆራረጥኩት እንዲያውቅልኝ መግለፅ እወዳለሁ።

"እግዜርን እሰሩት" የተሰኘው ግጥም ፖለቲካዊ ይዘት የተላበሰ ሲሆን ማህበረሰባዊ ጉዳዮችን በማንሳት የአስተዳደር ስርዓቶች ፖለቲካዊ ቀውሶች፣ የአምባገነንነት ጥጉ የእብሪተኝነት ልኬት፣ የተበላሸ ስርዓትና አስተዳደር ባህሪው እምቅ ቃላት በመጠቀም ለመግለፅ ይሞክራል።

**ስለ ግጥሙ ርዕሱ**

የግጥሙ ርዕስ ገና ከጅምሩ ብዙ ስለ ግጥሙ ይነግራል። የእግዜር ሀያልነት ከማንም የተሰወረ አይደለም የአምላክ አዛዥነት ከፀሀፊውም ሆነ ከአንባቢው ፈጽሞ የራቀ አይደለም ግን እንዲህ ብሎ ጀመረ "እግዜርን እሰሩት" ብሎ የሚያዝ የትኛው ሀያል አካል ነው? አምላክን እሰሩት ብሎ የሚል ከየት የተገኘ የአምላክ የበላይነትን የናቀ ወይም ካህዲ ሊሆን ይችላል። ምን ሊሆን ይችላል? አምላክን እሰሩት ብሎ የሚያዝ ደፋር ብሎ ማንነቱን ለመረዳት መሞከር ይገደዳል። የግጥሙ ርዕስ ሳቢና ለማንበብ የሚጋብዝ ነውና አንባቢው ገና ከጅምሩ የግጥሙን ርዕስ አይቶ ግጥሙን ለማንበብ እራሱን ይጋብዛል።

ስለዚህ ለግጥም "ርዕስ" መረጣ ወሳኝ መሆኑን የተገነዘበ ይመስላል ደራሲው። ርዕስ ሲመረጥ አንባቢ ሊጋብዝ የሚችል ሊያመራምርና መልስ ለመፈለግ የሚጋብዝ መሆን ይገባዋልና ይህ ርዕሱን የተዋጣለት አድርጎታል። እኔም በግጥሙ ውስጥ ያለው እግዜርን እሰሩት ያለው ደፋር ማንነቱን ለማረጋገጥ ግጥሙን ለመመርመር ገባሁ። ይሄው...

**እግዜርን እሰሩት**
**ከስሩ ታድሞ...ትውልድ ይማከራል..**
**"እና ምፅ" እያለ፣**
**ቁረጡት ያን ዝግባ- ምናባቱ ቆርጦት...**
**ለህዝብ ጥላ ጣለ!?**
**ወንበር ሲገረሰስ-ሳገር ጣይ ሲያወጣ...**
**ጥላው ስር ተቀምጦ... ህዝብ ከመከረ፤**
**ዝግባ አሸባሪ ነው..በግንደ ልቦናው**
**ሳጥናዔል ያደረ!**
**........—**

ዝግባ የታላቅነት ምልክት ነው። የአጋር አድባር የሂነ ሰውን ሽምግልና ይወከላል። ግጥሙ በጥሬ ትርጉሙ ሰዎች በዝግባ ጥላ ስር ሆነው መክረው አመፅ ያስነሳሉና የሚጠለሉበት ባለ ጥላው ዝግባ ይቆረጥ የሚል ይመስላል። ግን ፈፅሞ ትርጓሜው የተለየ ነው። በሀገሩ ላይ ያሉ እድሜ ጠገቦች ታላላቆች የሀገር አድባሮች። መልካሙን በመምከር እኩዩን በመኮነን በማረቅ ከዕድሜ ያገኙትን ለሌላ በመልካምነት የሚያወርሱ ታላላቅ ሰዎችን ይወክላል። እነዚያ ሰዎች ሸፍጥን በቀላሉ ይለያሉ፤ተንኮልን በእድሜያቸው ያወቁታልና ህዝባቸው እንዳይጎዳ ይህ መልካም የሆነ ነው ብለው ይነግራሉ። ያን የማይወድ ደግሞ እነዚያ የአገር አድባሮች መጥፋታቸውን እጅጉን ይገልጹታል። በግጥሙም የተጠቀሰው ሚስጥራዊ ቅኔ ይህንን ያመላክታል።

**—.........**
**እሰሩት!!**
**ይጨፍጨፍ ባህር ዛፍ**
**ምን ቅብጥ አድርጎት**
**ማገዶ እየሆነ እንጀራ አበሰለ፣**
**ስንቴ እየገደልነው የሞተ ግንዱ ላይ**
**ሌላ ነፍስ ፀደቀ..እልፍ ሆኖ በቀለ?**
**እንጀራ በወጡን በልቶ እየጠገበ**
**"ስራ ፈት ሰልፈኛ" መንገድ ካጣበበ**


እዚህ ስንኝ ላይ የላቀ ምልከታ ማህበራዊ እይታ የተለየ ሽሙጥ በእኛ በእያንዳንዳችን በዛሬዎቹ ላይ ተነስቷል። ለአገር ዋልታ ለወገን ጥላ የሆኑ መልካም ነገሮቻችን ሁሉ በእንቢታ መገፍተራችን ለእኛ የሚበጁ ለህዝብ የሚጠቅሙ እሴቶቻችን ማህበረሰባዊ እውቀትና ልማዶችን ሁሉ መቃረናችን የሚበጁንን አይበጁንም ብለን መኮነናችን ያነሳል።

**—... ሽብር ነው ባህር ዛፍ ፅድና ግራሩ**
**ከየበቀሉበት እየተለቀሙ**
**የዛፍ ዘር በሙሉ ከ'ሳት ይወርወሩ**
**ስሩ እየተማሰ ቅጠላ ቅጠሉ እየተበጠሰ**
**ለሕዝብ ጤና ሰጠ፤**
**በማህበር ስናብድ ጤነኛ በቅሉብን**
**መንጋው ተናወጠ**
**ከዚህ በላይ ሽብር ከዚህ በላይ ረብሻ፣**
**አሳፊ አግዳሚውን..ስለምን ይንከሰው...'**
**እውነት' እንደውሻ..."**

በየጉዳዮቻችን ላይ በማህበር በደቦና በአንድነት መላ ቅጡ እንደጠፋብን ሁሉ የምነሆነውን በእብደት ስሎ የእውነት ተግባርና ሁኔታችን ሁሉ የእብድ መሆኑ ያመላክታል። እንደግለሰብ ትክክለኛ መስመርና አቋም መያዝ ሲያስወቅስ፤ በጎ ነገር ላይ መቆማችን በህብረት ስያስወግዘን ተመለከተና በጋራ ማበዳችን በጎ

**እንደሆነ አድርጎ በአሽሙር ያወግዘናል።**
**ማን አብዶ ማን ሲቀር... አናብድም "ምትሉ?**
**አርፋችሁ እበዱ "ሽብርተኞች" ሁሉ!**
**መንጥሩት ቅጠሉ ከተቀበረበት ስራስር ይመዘዝ፣**
**"መድሀኒት ነኝ" የሚል ይወገር**
**ይሰቀል በደቦ ይወገዝ!**
**......"**

በእያንዳንዱ አገራዊና ማህበረሰባዊ ጉዳይ ላይ የምንሄድበት የምናይበትና የምንቆምበት ጉዳይ ሁሉ መስተካከል እንዳለበት ለእኛ በጎ የተባለ ለመኖራችን ወሳኝ የሆነ ለህልውናችን እጅጉን አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ መተዋቸን በአንድነት እብደት ላይ መገኘታችን ያመላክታል። በእርግጥ ዛሬ እርጋታ የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ነን። በእርግጥም አሌክስ አብረሀም ያየበት መነፅሩ እኛን በትክክል ያየበት መሆኑ ማመሳከሪያው ዛሬ ላይ የምንሆነውና የሆነው ትልቅ ማስረጃ ነው።




ግጥሙ ቀጠለ...

**—የታባቱ!**
**እሰሩት በሬውን! እኛ ሳንፈቅድለት**
**ምድር እያረሰ፣**
**ሥጋውን ጆብቶ ...ጥሬውን ከብስል...**
**ህዝብ እያጋበሰ**
**ህዝበ በሳተኛ...በየ በረንዳው ሳይ ...**
**በሚስለው ቢላ፣**
**ይበላው ያጣ ቀን እኛን እንዳይበላ**
**ራብን ይጥገባት...ከዳቦ በስተቀር...**
**እንዳያስብ ሌላ**
**ሳሩን እጨዱና በሬውን እሰሩት፣**
**መደለብ ሽብር ነው የደለበን ቀንዳም**
**ጨማውን ትታችሁ...እርሻውን ትታችሁ..**
**ውጊያውን አግንኑት!"**

እርግጥለኛየሚገባውስርነቀልለውጥ፤አስተማማኝ በራሳችን የሚያቆመን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሆኖ ሳለ እንደማህበረሰብ ዋንኛ ፍላጎታችን የሚያስፈልገንን አርቆ የማያስፈልገን ላይ ትኩረት ማድረጋችን በዚህ ስንኝ ማሳየቱን ቀጥሏል። ማህበረሰባዊ ዝንፈታችን የማይበጀንን መስመርና ሂደት ላይ መሆናችንን ማሳየቱን ግጥሙ አላቆመም። ለእኛ የተሻለው የቱ እንደነበር ነገር ግን ምርጫችን ምን እንደሆነ ያሣየናል። በእርግጥ ግጥሙ የታተመው ስንኙ የተቋጠረው ዛሬ ባይሆንም ለአሌክስ ግን ትናንት ጥበብ አሻግሮ ዛሬን እንዲያይ አድርጎት ነበርና ያኔ ያየው ዛሬ ከቆምንበት ጋር ገጠመ። እናም በዚህ ግጥም የዛሬ ሁኔታችንን ተመለከትን።

**"እሰሩት!!**
**ንፋሱን እሰሩት ማንን አስፈቅዶ**
**እንዳሻው ነፈሰ፣**
**ህዝቡስ ካለ ፍቃድ ለምን ተነፈሰ?**
**እሰሩት አየሩ መታፈን ነው ደጉ፣**
**የታፈነ ትውልድ... ጩኸት አያበዛም...**
**በየጥጋጥጉ!**
**"ሺ ዓመት ንገስ" የሚል ምድሩ ይፈንጭበት፣**
**"ለምን" ባዩ መቶ...**
**"እንዴት"ባዩ "በጥባጭ'**
**ይቆምበት ይጣ... "ቅድስት' ምድራችን**
**እሳት ይሁንበት!!**
**ሰቅዞ ይዞናል...የራሳችን ድግስ...**
**የራሳችን ተስካር**
**መድረሻህን ፈልግ -'ሰላማዊ ስካር'**

እዚህ ስንኝ ላይ በወቅቱ የነበረውን አገራዊ ገፅታችን በጊዜው የነበረውን ፖለቲካዊ ገጽታ ቅልብጭ አድርጎ ያሳያል። በአገሪቱ በነበረው ፖለቲካዊ ስርዓት መበደልና ጭቆና ያንገሸገሻቸው ስርዓቱን ሲቃወሙ ይደርስባቸው የነበረው እስራት እንዲሁም ተገቢ ያል ሆነ የሙብት መገፋት አጉልቶ ያሳያል።

**እሰሩት!**
**እ...ዛ ሳይ...**
**ድንገት ሳይደፋብን የአብዮት ዝናብ...**
**የብጥብጥ መና፣**
**ከሰማይ ሰማይ...ተገፎ ይታጎር...**
**ይቀፍደድ ደመና**
**በዚች "ቅድስት' አገር እንኳን**
**ያመፅ ጥሪ እንዳይኖር ትንታ**
**ከስር ያመለጠች የዝናብ ዘለላ-የውሀ ኮለልታ፣**
**እንጦሮጦስ ትውረድ በፍኝ ተጠራቅማ...**
**በፎሌ ተሞልታ**
**ድንጋይ ትበሳለች...ሳይን አትሞላም**
**ብስን የናቅናት ጠብታ!**
**ትታሰር!!**

ግጥሙ የወጣበት እና ከዚያ በፊት የነበረው አገራዊ ሁኔታ ያሳያል። የወቅቱን ስርዓት (ኢህአዴግ) ይቃወማል አልያም ስርዓቱን ይፈታተናል ያለው ሁሉ በየ ምክንያቱ ያስር ነበርና ደመናውም ሳር ቅጠሉ ሁሉ ይታሰር ምክንያቱም በጣም ተቃዋሚ ነውና ብሎ በሽሙጥ የስርዓቱን ስራ ይኮንናል።ታቃዋሚ የተባለ ሁሉ ይደርስበት የነበረው መከራ፤ አመፅና የህዝብ ተቃውሞ እንዳይነሳ ለማድረግ ይደረጉ የነበሩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ይዘረዝራል።

.......

**ሰማይ ባዶ ይሁን**
**ከ'ኛ እግዜር በቀር ማንም እንዳይረግጠው**
**"ፀሀይ የት ደረሰች ጨረቃ የት ገባች'**
**የሚል ጠያቂ ነፍስ ...መቼም እንዳይገልጠው!**
**ይከደን ሰማዩ- ጨለማ ይዋጠው!**
**በጨለማ ሰማይ በድቅድቁ ህዋ የተጠራቀመ፣**
**ይታሰር ኮከቡ አንድ ባንድ በነቂስ እየተለቀመ!**
**መሬቱም ይታረስ አዳሜ ሚረግጠው፣**
**ሽብርተኛ ደም ነው ሲጠጣ የኖረው፣**
**አፈሩን ብትገልጠው**
**ይመስልሀል እንጂ የስጋጃ ምንጣፍ**
**ሸፍኖት ሳር ቅጠል ሸፍኖት አበባ፣**
**ነገ ቀን ሲከዳ በቁምህ የሚውጥ**
**ክፉ መቃብር ነው ካፈር የሚያስገባ**

አፈሩ አፍ አውጥቶ አይናገርም፣ ምድሩ ልሳን አበጅቶ አያወራም፣ሰማዩ ሰው አይደለምና ምንም ቢሆን ተው አይልም እዚህ ላይ በተምሳሌታዊ ዘይቤ የሚጠቀሱት ሰዎች ናቸው ሰማይነትና መሬትነት ተላብሰው የሚተነፍሱና ምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች ናቸው። ነገር ግን ሳር ቅጠሉ ታዳኝ ነበርና አዳኙ ምንም እንደማይለይ በአንድነት ሁሉም ላይ ስቃይ እስርና ያመላክታል። ለተቃውሞና ለስርዓቱ ፈተና እንዳይሆን ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠር የሚሰራውን ተግባር በዘይቤ ይወርፋል።

**እሰረው!!**
**እንደውም... ሰማዩ ይታረስ ...**
**ተጠቅልሎ ይግባ እንደ ሰሌን ምንጣፍ፣**
**ቀና እንዳይል ህዝቡ-የነጻነት ምኞት-በላዩ**
**እንዳዓፈ! ሰማይ ሸቤ ይውረድ...**
**እግዜር ለዙፋኑ ቦታ ሲቸግረው፣**
**ይወድቃል ከጻችን...በደረቅ እንጨት**
**ላይ ግራ ቀኝ ቸንክረው!**
**በቃ! ምድርን ከቀፈደድክ... እግዜርን ካሰርከው፣**
**ህዝብና ህዝቤን..."ኢትዮጵያ እጆችዋን"**
**እያልክ ስበከው**
**የታሰረች አገር...ወዳሰርነው አምላክ-እጇን**
**ብትዘረጋም፣**
**ይህን ሁሉ ደክመን... ያቆምነው ጨለማ...**
**በቀላሉ አይነጋም!!**
**......../.../......**

እዚህ ላይ የማያደርጉትን ሀያል ተግባር የማይሚገቱትን ትልቁን ዙፋን አምላክነት በሰውኛ ልኬት ተለክቶ መታሰር የታወጀበት መሆኑ ሲታይ እንዴት ይባል ይሆናል። ነገር ግን ህልውናው ለሚጠራጠር እሱን ማሰር ይቀለዋልና ከሱ በላይ ነኝ ብሎ ለሚያስብ አልያም በአምላክነቱ ለማይቀበለው አምላክ ለሱ ምኑም ነውና የናከውን ትዕዛዙ ያልተገበርከውን ምንም አድርግ እንደማለት ።

በመጨረሻም መራር እውነት ነግሮ ዝንኙን ይቋጫል። በዚህ ሁሉ ተግባር ውስጥ ታልፎ በዚህ ሁሉ እኩይ ተግባር ውስጥ ተቆይቶ መልካም ነገር ላይ ለመድረስ እንደሚያስቸግር ነግሮ ያበቃል። በጎነት ካልቀረበ መሄጃውና አካሄዱ ካላማረ መድረሻው ይቸግራልና የወቅቱን ሁነት ከባድነት ዛሬ ላይ ተገልጦ እንደታየ ሁሉ በመጠቆም ምግባር ውስጥ የበለጠ መጥፎነት ጎልቶ ይወጣልና ተግባሩ ይቁም ካልሆነ ግን ይከፋል ብሎ አበቃ። እኔም አበቃሁ፤ ቸር ያሰማን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ፈጣንና መፍትሔን የሚሻው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ችግር

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በዓለም ላይ ቁጥራቸው ከአንድ ቢሊዮን የሚበልጡ የአካል ጉዳተኞች እንዳሉ የዓለም ባንክ እና የዓለም ጤና ድርጅት መረጃዎች ያሳያሉ።ባለፈው ዓመት ይፋ በተደረገ መረጃ በኢትዮጵያም ከ20 ሚሊዮን በላይ አካል ጉዳተኞች እንደሚገኙ መገለፁ ይታወሳል።

የአካል ጉዳተኞች ችግር ከሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር ሲነፃፀሩ በቁጥር የበዛ፣ በዓይነትም ውስብስብ መሆኑ ተደጋግሞ ይነገራል።በድሃ አገራት ያለው የአካል ጉዳተኞች ችግር ደግሞ እጅግ አስከፊና አሳዛኝ ሲሆን፤ መነሻውም ምጣኔ ሀብታዊ መሆኑ የጋራ ስምምነትን ያገኘ ጉዳይ ነው።

የአካል ጉዳተኞችን ሕይወትና ኑሮ ከባድ ከሚያደርጉ መሰናክሎች መካከል አንዱ የኅብረተሰቡ አመለካከት ሲሆን፤ ስለአካል ጉዳተኞች ያለው የተዛባ ማኅበረሰባዊ አመለካከት አካል ጉዳተኞች በኅብረተሰቡ ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ እንዳይሆኑ ሲያደርጋቸው፤ በአካል ጉዳተኛነታቸውም ከማኅበረ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞችና አገልግሎቶች በብዙ መልኩ ሲገለሉ ይታያል።መገለላቸው ደግሞ በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ከፀደቁ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ውጭ ያደርጋቸዋል።ይህ በበኩሉ ለአስከፊ የስነ ልቦና ቀውስ ያጋልጣቸዋል፡፡

ማኅበረሰቡም ሆነ መንግሥት ትኩረት ሰጥተው እንዲያከብሩት በዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ከተጠቀሱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ትምህርት የማግኘት መብት ነው።አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው የትምህርት እድል አግኝተው ተምረው ራሳቸውን ብሎም ማኅበረሰባቸውና አገራቸውን እንዲጠቅሙ ይጠበቃል።ለዚህ ደግሞ ምቹ ሁኔታዎች ሊፈጠሩላቸው እንደሚገባ በእነዚሁ ስምምነቶችና የትግበራ ማስፈፀሚያ ሰነዶች ላይ ተጠቅሷል።ይሁን እንጂ በአገራት ኢኮኖሚያዊ አቅምና ማኅበረሰባዊ አመለካከት ምክንያት ይህ ችግር እየባሰ እንጂ እየተፈታ ሲሄድ አይታይም።

ኢትዮጵያ አሁን የምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ደግሞ ጉዳታቸው ከዚህ የባሰ እንዲሆን አድርጎታል።የሰላም እጦት፣ የወረርሽኝ መስፋፋት እንዲሁም የኑሮ ውድነት ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› እንደሚባለው ተደራራቢ ችግሮቻቸው ከሆኑም ሰነባብቷል።ጦርነቱ ያስከተለው መፈናቀል አካል ጉዳተኞች በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ከቷቸዋል።እየተከታተሉት የነበረውን ትምህርት ጭምር እንዲያቋርጡ አስገድዷቸዋል።በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ ከቀድሞ መኖሪያቸው ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመሄድ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ጥረት አድርገዋል።ይህ ጥረታቸው ግን ከላይ በተጠቀሱት የአካል ጉዳተኞች ችግሮች ምክንያት በርካታ መሰናክሎች ያሉበት ነው፡፡

ይህንን በተመለከተና መሰል የአካል ጉዳተኞችን ችግር በምን መልኩ ለመፍታት እየጣረ እንደሆነ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አገልግሎት ከሚሰጡ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ በሆነው፤ ሰባት ዓይነ-ስውራንና ሁለት መስማት የተሳናቸው መምህራን እንዲሁም 39 ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ወደ'ሚገኙበት ዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገኝተን የተወሰኑ ክንውኖችን ለመዳሰስ ሞክረናል።

የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ ኤፍሬም ምትኩ እንደሚሉት፤ አገር ችግር ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ እንደ ትምህርት ቤት በተለያየ መልኩ ማገዝ ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው።በመሆኑም ትምህርት ቤቱ ተፈናቅለው የመጡ 150 ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ ላይ ይገኛል።ከእነዚህ መካከል ደግሞ የአካል ጉዳተኞች በመኖራቸው በልዩ ሁኔታ የሚደገፉበትን ነገር ተመቻችቷል።ከዚያ በተጨማሪ ነባር አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለማገዝ የሚችሉ አራት የልዩ ፍላጎት ባለሙያዎችን፤ ሁለት የማማከር ሥራ የሚሠሩና ሁለት በልዩ ፍላጎት ዙሪያ የሰለጠኑ መምህራንን ቀጥሮ ተማሪዎቹ አገልግሎቱን እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ነው።

ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎችን ከመለየትና አስፈላጊ የድጋፍ ግብዓቶችን ከማሰባሰብ ጀምሮ ድጋፉ የሚመራበትንና የሚቀርብበትን አሠራር እስከመዘርጋት የደረሰ ተግባር በትምህርት ቤቱ እንደሚከናወን የሚያነሱት አቶ ኤፍሬም፤ እስካሁን ድረስ የተከናወኑት ተግባራት ውጤታማ መሆናቸውን ያስረዳሉ።ሌሎች ተቋማት ከትምህርት ቤቱ ተሞክሮ ወስደው መሰል ሥራዎችን እንደጀመሩም ያብራራሉ።እንደውም ድጋፍና እንክብካቤያቸው ጥሩ ስለሆነ በቅርቡ ከጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት ሁለት ተማሪዎችን እንደተቀበሉም ይናገራሉ።

በትምህርት ቤቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዋ ወይዘሮ ከበቡሽ ብሩክ በበኩላቸው፤ ተማሪዎቹ እያጋጠሟቸው ስላሉት ችግሮች ያብራራሉ።የመጀመሪያ ብለው ያነሱትም መንግሥት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራን ቋሚ ቅጥር አለመፈጸሙን ነው።የምልክት ቋንቋ ትምህርት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ይሰጣል።ነገር ግን የቅጥር ሁኔታው በቋሚነት አይደለም።ይህ ደግሞ በሙያው የተመረቁ ባለሙያዎች መደበኛ/ቋሚ በሆነ ጊዜና ቦታ እንዳይሠሩ (አካል ጉዳተኞችን እንዳያገለግሉ) አድርጓቸዋል፡ ኮንትራት መሆኑ ደግሞ በየጊዜው እንዲቀያየሩ ያደርጋል።በመሆኑም ተማሪዎች በሚፈልጉት መልኩ እንዳይማሩ ሆነዋል።ስለዚህ እንደማንኛውም የመምህራን ቅጥራቸው በቋሚነት እንዲሆን ሊመቻች ይገባል በማለት ያሳስባሉ።

‹‹አሁን በትምህርት ቤቱ ካሉት ተማሪዎች በተጨማሪ ሌሎች ተማሪዎችን ብንቀበል አገልግሎቱን መጠቀም የሚፈልጉ በርካታ ናቸው" የሚሉት ባለሙያዋ፤ አዲስ አበባ ማዕከል በመሆኑ ሁሉም ሰው ይፈልገዋል፤ በሌሎች ክልሎች ይህን አገልግሎት የሚሰጡ ብዙ ትምህርት ቤቶች የሉም።ስለሆነም እንደነዚህ አይነት አገልግሎቶች ሁሉም በአቅራቢያው ሊከፈትለት እንደሚገባም ይናገራሉ።


የአካል ጉዳተኞች ችግር ተዘርዝሮ አያልቅም የሚሉት ወይዘሮ ከበቡሽ፤ በሦስተኛ ደረጃነት ያነሱትና አንገብጋቢ ነው ያሉት ጉዳይ የምገባ ሥርዓቱን በተመለከተ ነው።‹‹መንግስት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኞች ብቻ ሳይሆኑ የአካል ጉዳት የሌለባቸው ተማሪዎችም ጭምር ምግብ የሚያገኙበትን አማራጭ አመቻችቷል።ይህም ጥሩ እድሎችን የፈጠረ እንደሆነ ይታወቃል።በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግን ይህ ሲደረግ አይታይም።

ብዙ ትግሎችን ተጋፍጠው ለስኬት የቀረቡት እነዚህኞቹ ናቸው።ነገር ግን በብዙ ነገር ድጋፋቸው እየቀነሰ መጥቷል።ከአካል ጉዳተኞች አንጻር እንኳን የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው።ስለሆነም ከአቅም አንፃር ሁሉንም ተደራሽ ማድረግ ባይቻልም አካል ጉዳተኞች በምገባ መርሐ ግብሩ ማካተቱ ግን ለነገ መባል እንደሌለበትም ያነሳሉ።ተማሪዎቹን መደገፍ ቢቻል ከራሳቸው አልፈው ለአገራቸውም የሚጠቅሙ ዜጎችን ማግኘት ይቻላልና የትምህርት ጉጉታቸውን በሚያስፈልጋቸው ቦታ ደርሶ ማሳካት እንደሚገባም ያሳስባሉ።

ወይዘሮ ከበቡሽ የሚጠቅሱትና ትኩረት የሚያሻው ሌላው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ችግር የመኖሪያ አካባቢ ጉዳይ ነው።እሳቸው እንደሚሉት ከሆነ በጋራ የሚኖሩበት አካባቢ ተዘጋጅቶላቸው የሚረዳዱበትና ራሳቸውን ከችግር የሚታደጉበት አማራጭ እንዲመቻችላቸው ቢደረግ የሚል ምክረ ሀሳብ ያቀርባሉ።በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተሞች ይህንን ተግባር መከወን እንደሚችሉ ያምናሉ።ለአብነት ያህል የተማሪዎቹን መኖሪያ በቀበሌ ቤቶች አድርጎ በሰርቪስ የሚመላለሱበት እድል ቢመቻችላቸው ብዙ ችግሮቻቸውን መፍታት ይቻላል።ለዚህ ደግሞ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም እገዛ ሊያደርጉ ይገባል።

አካል ጉዳተኝነት በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ሰው ላይ ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው።እያንዳንዱ ሰው ነገው ምን እንደሚሆን፤ ምን ይዞ እንደሚመጣ አያውቀውም።እናም እገዛውም በዚያው ልክ መታየት አለበት የሚሉት ባለሙያዋ፤ ስለአካል ጉዳተኞች የሚስተዋለው የተዛባ አመለካከት ባልተስተካከለበትና ትክክለኛ ግንዛቤ ባልተያዘበት፣ አድልኦና መገለል ባልተወገደበት፤ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞችና ችግሮቻቸው የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በሆነበት ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ አካል ጉዳተኞች ከድህነትና ከተጎሳቆለ አኗኗር ይወጣሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።ስለሆነም አመለካከትን ማስተካከልና ትኩረትን ማሳደግ የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የሁሉም ሰው ግዴታ እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል እኛልን ለዛሬ አበቃን።ሰላም!

# ዓለም አቀፍ



## ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የምሥራቅ አፍሪካን ማኅበረሰብ ተቀላቀለች

አዲስ አበባ ፤ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የምሥራቅ አፍሪካን ማኅበረሰብ ለመቀላቀል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ ተገለጸ፡፡

ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የቀጠናው አገራት ዜጎች ያለገደብ በመንቀሳቀስ በሚያከናውኗቸው ነፃ የግብይት እና የንግድ ትሥሥር ተጠቃሚ ትሆናለች ተብሏል፡፡

የምሥራቅ አፍሪካ ማኅበረሰብ ሊቀ መንበር እና የኬንያው ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ በመሩት የበይነ-መረብ ጉባዔ ላይ ÷ "የዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ወደ ቀጠናዊ ማኅበረሰቡ መቀላቀል በቀጠናዊ ውህደቱ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ክስተት ነው" ማለታቸውን የዘገበው ሲ ጂ ቲ ኤን ነው፡፡

## ሩሲያ 10 የተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶች ሞስኮን ለቀው እንዲወጡ አዘዘች



አዲስ አበባ፣ ሩሲያ 10 የተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶች በ72 ሰዓታት ውስጥ ሞስኮን ለቀው እንዲወጡ ማዘዟ ተሰምቷል፡፡

ዲፕሎማቶቹ የሞስኮን ገጽታ ለማበላሸት ተንቀሳቅሰዋል በሚል ነው ከሩሲያ እንዲወጡ የታዘዙት፡፡

ከሩሲያ እንዲወጡ የታዘዙትም የኢስቶኒያ፣ላቲቪያ እና ሊውትኒያ ዲፕሎማቶች መሆናቸው ተገልጿል፡፡

የሊውትኒያ አራት የኤምባሲ ሰራተኞች፣ ሶስት የላትቪያ ኤምባሲ ዲፕሎማቶችን እንዲሁም ሶስት የኢስቶኒያ ተወካዮችን በድምሩ 10 ዲፕሎማቶችን ከሞስኮ እና ከሴንት ፒተርስበርግ እንዲወጡ መታዘዛቸውን የሩሲያ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

ሩሲያ በዩክሬን ላይ ባደረሰችው ወታደራዊ ጥቃት በምዕራቡ ዓለም እና በሞስኮ መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ጦርነት በከፍተኛ ሁኔታ የተባባሰ ሲሆን በርካታ የአውሮፓ አገራት ቀደም ሲል የሩሲያ ዲፕሎማቶችን አባረዋል፡፡

በዚህ ወር ፖላንድ በስለላ የጠረጠረቻቸውን 45 የሩሲያ ዲፕሎማቶች ከአገሯ ያስወጣች ሲሆን በተመሳሳይ ቤልጂዩም፣ አየርላንድ እና ኔዘርላንድስ በድምሩ ከ40 በላይ የሩሲያ ዲፕሎማቶችን ከአገራቸው አባረዋል፡፡

ከውሳኔው በኋላ የሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ የሩሲያ ዲፕሎማቶች መሠረተ ቢስ መባረር ተገቢ ምላሽ ያገኛል ብሏል፡፡

የላትቪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤድጋርስ ሪንኬቪክስ በበኩላቸው የሩሲያ ባለስልጣናት የአገራቸውን ዲፕሎማቶች ያለምክንያት ማባረራቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዩክሬን እና ሩሲያ ጦርነት ጋር ተያይዞ ምዕራባውያን አገራት ዲፕሎማሲያቸው እየተቀዛቀዘ መሆኑን አር ቲ በዘገባው አመላክቷል፡፡

# ስፖርት



## ልዑኩ አቀባበል ተደረገለት

ብርሃን ፈይሳ

ጥንታዊ መሠረት ካላቸው ስፖርቶች መካከል አንዱ ፈረስ ስፖርት ነው። ይህ ስፖርት በርካታ የውድድር ዘርፎች ያሉት ሲሆን፤ እአአ ከ1900 ጀምሮ ከኦሊምፒክ ስፖርቶች መካከል አንዱ ሊሆን ችሏል። ይህ ስፖርት በኢትዮጵያ ከጥንታዊና ባህላዊ ስፖርቶች መካከል ይመደባል። በአገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች በዓላትን ተንተርሰው ከመካሄዳቸው ባለፈ በኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ዕውቅና ካገኙና ውድድርም ከሚካሄድባቸው ስፖርቶች መካከል አንዱ ነው።

ከዚህ ባሻገር በሌላው ዓለም የሚዘወተረውና ዘመናዊ የሆነው ስፖርት በኢትዮጵያ ፈረስ ስፖርት አሶሴሽን አማካኝነት ይካሄዳል። በአገሪቷ ከሚገኙ ስምንቱ የስፖርት አሶሴሽኖች መካከል አንዱ የሆነው ፈረስ ስፖርት የተለያዩ ክለቦችን በስሩ ያቅፋል። በተለያዩ ጊዜያት በአሶሴሽኑ አዘጋጅነት በጃንሜዳ በሚካሄዱ ውድድሮች ላይም ከክለቦቹ ባሻገር ኤምባሲዎችና የውጪ አገራት ዜጎችንም በማሳተፍ ይታወቃል። በርካታ የፈረስ ዝርያዎች ያሏት አገሪቷ ለስፖርቱ ምቹ ሁኔታዎች በስፋት መኖራቸውም በባለሙያዎች ይነሳል።

ኢትዮጵያ በፈረስ ሃብት ከመታደሏ ባለፈ፤ በመጓጓዣነት፣ በጦር እንዲሁም በመዝናኛነት ሰፊ ድርሻ አለው። ይሁንና አገሪቷ እስካሁን ካልተጠቀመችባቸው ሃብቶቿ መካከል አንዱ መሆኑን ተከትሎ እንቅስቃሴውም ከአገር ውስጥ እምብዛም ያልዘለለ ሆኖ ቆይቷል። ከሰሞኑ በአፍሪካ ደረጃ በተካሄደ አንድ ውድድር ግን በስፖርቱ አዲስ ታሪክ እንዲሁም አበረታች የሆነ ተስፋ ታይቷል። በሰሜን አፍሪካዊቷ አገር አልጄሪያ አስተናጋጅ በሆነችበት አህጉር አቀፍ የፈረስ ስፖርት ሻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያዊው ታዳጊ ለአገሩ ሜዳሊያ ሊያስመዘግብ ችሏል። በውድድሩ ላይ አገሩን ወክሎ የተሳተፈው ብሔራዊ ቡድን ወደ አገሩ ሲመለስም አቀባበል ተደርጎለታል።



በፈረስ ስፖርት የታዳጊ ወጣቶች ዘርፍ ኢትዮጵያ ታሪካዊውን ድል አስመዝግባለች፤

ኢትዮጵያ በሻምፒዮናው ላይ ውድድር ከሚካሄድባቸው የሕጻናትና የታዳጊዎች ወጣቶች ዘርፍ ተሳታፊ ስትሆን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ከኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የተገኘው መረጃ ያስረዳል። እድሜቸው ከ18 አመት በታች የሆኑ 7 ታዳጊዎች በብሔራዊ ቡድኑ ታቅፈው አገራቸውን የወከሉ ሲሆን፤ ላለፉት ሁለት ዓመታት በውድድሩ ተካፋይ ለመሆን አሶሴሽኑ ሲዘጋጅ ቆይቷል። ከመጋቢት 14-16/2014 ዓ.ም በተካሄደው ውድድርም ከ12-14 የዕድሜ ክልል በተካሄደው የመሰናክል ዝላይ ታዳጊው ፈረሰኛ ፈጠነ ተሾመ አሸናፊ በመሆኑ ለአገሩ የወርቅ ሜዳሊያ አስገኝቷል። የቤካ ፈርዳ ክለብ ጋላቢው ፈጠነ በአገር ውስጥ በሚካሄዱ ሻምፒዮናዎች ተሳትፎውም በውጤታማነቱ ይታወቃል።

ውጤቱ ተስፋ ሰጪ በመሆኑም ልዑኩ ወደ አገሩ መመለሱን ተከትሎ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጀላ መርዳሳ፣ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር መስፍን ቸርነት እንዲሁም የአሶሴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል አድርገዋል። በአቀባበሉም ላይ ሚኒስትሩ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በታሪክ በፈረስ ግልቢያም ሆነ በፈረስ ውጊያ በጦር ሜዳ ብዙ ታሪክ የሠራች በመሆኑ በዚህ ውድድር ታሪክ የተደገመበት ታላቅ ጀብድ መሆኑን ገልጸዋል። እንደ ፈረስ ስፖርት አሶሴሽን ውጤታማ የሆኑ የስፖርት ማኅበራትን ወደ ስፖርት ማዕከል ለማስገባት መንግሥት በትኩረት እንደሚሠራም መጠቆማቸውንም ሚኒስትሩ በድረገጹ አስነብቧል።

የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር ቸርነት በበኩላቸው፤ ‹‹ኢትዮጵያውያን ከፈረስ ጋር ወጥተው ተሸንፈው አይመለሱም፤ የጊዜና የቴክኖሎጂ ልዩነት ቢኖርም አባቶቻችን በወጡበት መስክ ሁሉ ከፈረስ ጋር ታሪክ ሠርተው እንደሚመለሱ ይህ አንዱ ማሳያ ነው›› ብለዋል። አምባሳደሩ አክለውም የፈረስ ስፖርት አሶሴሽን በአፍሪካ መድረክ በውጤት መጀመሩ የሚበረታታ ስለሆነ ሁሉም ብሔራዊ ፌዴሬሽኖች የመጨረሻ ግብ የአገር ባንዲራ ከፍ አድርጎ ማስጠራት እስከሆነ ድረስ ተግተው ሊሠሩ ይገባል። መንግሥት የተገኘውን ድል መነሻ በማድረግ በሌሎች ውድድሮችም ጠንካራ ሆነው እንዲገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግም አስረግጠዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

### ገጨ.ቁ ESLSE/KBPT/002/2014

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች የቀረቡትን የተለያዩ የወደብ ማሽን የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ጎማዎች ማቅረብ ከሚችሉ ድርጅቶች አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም በጨረታው ስመሳተፍ የሚፈልጉ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማሟላት መጫረት የሚችሉ መሆኑን ይገልጻል፡፡**

1. በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች የታደሰ የንግድ ፈቃድ ፤ የተ.ዕ.ታ ሰርተፊኬት ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ አለባቸው፤
2. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ዋና እና ኮፒ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በአንድ ፖስታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፤
3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የጠቅላላ ዋጋውን 2% ያላነሰ በሲ.ፒ.ኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ ‹‹የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት (Ethiopian shipping and logistics service enterprise kality branch office)” በሚል ስም በማሰራትና በማቅረብ መጫረት ይችላሉ ፤
4. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ በሚገኘው የምድር ሚዛን መስተናገጃ ገንዘብ መቀበያ ቢሮ መውሰድ ይቻላል ፤
5. ጨረታው ‹‹ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት” ግዥና ንብረት አስተዳደር ክፍል ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ 16ኛ ቀን ከረፋዱ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ዕለት በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ፖስታው ይከፈታል ፤
6. ከጨረታው መክፈቻው ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፤
7. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በከፊልም ሆነ በሙሉ ጨረታውን የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ስልክ ቁጥር 011-888-92-22

**የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት**

**የቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት**

## Invitation to NCB Bid

For the Consultancy of Environmental and Social Impact Analysis of Land Fill and Resettlement Action Plan

The Sululta Municipality office funds a budget for the Consultancy of Environmental and Social Impact Analysis of Land Fill and Resettlement Action Plan 2014 EFYs.

1. The Sululta Municipality office now invites eligible EIA Consultant (Level I) which can fulfill the following mandatory documentary evidence for compliance.

I. The bidders need to have registered and renewed Consultancy trade license valid for the year 2014 E.F.Y.

II. The bidders have to be registered for VAT Certificate.

III. The bidders have the Tax Clearance Certificate issued by the Tax Authority at the time of bid submission date that permits the bidders to participate in any public tenders

IV. The bidders have to have at least three years experience with similar works and have the Completion certificate of the projects.

V. The bidders could be able to provide the necessary professionals.

2. Interested eligible bidders may obtain further information and inspect the bidding documents at Sululta Municipality office at the address given below from 2:30 to 6:30 and 7:30 to 11:30 from Mondays to Fridays at local time.

3. A complete set of Bidding Documents may be purchased by interested eligible bidders from first announcement date of this tender advertisement on News Paper for 15 calendar days at the below office described under upon payment of a non-refundable fee of Birr 500 Birr (five Hundred Birr Only).

4. Bids must be accompanied by a bid security of 50,000 Birr. The bid security can be submitted in the form of CPO or unconditional Bank guarantee.

5. Late bids will be rejected and Bids will be closed on 15th day from the date of announcement letter at 4:00 local time and shall be opened at 4:30 local time on the same day in the presence of bidders representatives who choose to attend, at the address below on

**Sululta Town Finance and Economic Co-operation Office**

**Tel 0111860367/68**

**Sululta, Oromia**

**7. Sululta Municipality reserves the right to accept or reject any or all bids**

**Sululta Municipality office**